‹‹ምን እላለሁ? ምንስ እናገራለሁ? ከዘመን
አስቀድሞ የነበረው እርሱ ሕፃን ኾኗልና። እኔ ፈጽሜ
አደንቃለሁ። ከሰማየ ሰማያት በላይ የሚኾን፣
በዘለዓለማዊ ዙፋን የሚኖር እርሱ በበረት ተጣለ።
ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

# ስምዐ ጽድቅ

## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች
፫ መልእክት
፭ ሪፖርታዥ
፮ ቤተ አብርሃም
፲ ቃለ መጠይቅ
፲፪ የሕፃናት ዓምድ
፲፫ ትዝብት
፳ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ




## ስምዐ ጽድቅ


የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ በጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442
✉ 80078
አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
newspaper@eotcmk.org



ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ
ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ
ሪፖርተር
ረቂቅ መቻል
የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነር
ግደይ ገብሬ
ጸሐፊ
ገነት ታደሰ

# በሀገራችን እየተከሠተ ያለውን አለመግባባት ለመፍታት ኅብረተሰቡ ማኅበራዊ አንድነቱን አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ ቀረበ

*በካሣሁን ለምለሙ*

በሀገራችን በየአቅጣጫው እየተከሠተ ያለውን አለመግባባትና ግጭት ኅብረተሰቡ በጥበብና በማስተዋል እንዲመለከተው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም በዓለ ልደተ ክርስቶስን አስመልክተው በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ጥሪ አቀረቡ።

እየተከሠቱ ያሉ አለመግባባቶች ግጭቶች ልማትን፣ ነፃነትንና፣ ሉዓላዊነትን የሚፈታተኑ በመሆናቸው ሁሉም ለሀገሩና ለሃይማኖቱ እንዲሁም ለወገኑ ተገቢ ትኩረት በመስጠት በጸሎትና በሚችለው ሁሉ ትብብሩን አጠናክሮ እንዲቀጥል ቅዱስነታቸው በመግለጫው ጠይቀዋል።

በሀገራችን የተከሠቱት አለመግባባቶች እየተካረሩ መጥተው ወደ ግጭት እንዳያመሩ የጠቆሙት ቅዱስነታቸው በግጭቶቹ ምክንያት የሰው ሕይወት እልቂት፣ ረኀብ፣ መፈናቀልና ሌሎች መኀበራዊ ቀውሶች እየተፈጠሩ እንደሆነም ተናግረዋል። ቅዱስነታቸው አያይዘውም የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝንና የኤች አይ ቪ ቫይረስ በሽታዎችን ለመከላከል ከቸልተኝነት መራቅ እንደሚገባ በመግለጫቸው አስገንዝበዋል።

በመጨረሻም የክርስቶስን ልደት ስናስብ ለእግዚአብሔር ክብር በመቆም ሰላምንም በመስጠትና በመቀበል ሊሆን ይገባል ያሉት ቅዱስነታቸው የታመሙና የታሰሩትን በመጠየቅ፣ የተራቡትንና የተጠሙትን በማብላት በማጠጣት፣ የታረዙትንም በማልበስ፣ ለእግዚአብሔርና ለወገን ያለንን ክብርና ፍቅር በመግለጽ በዓሉን ማክበር እንደሚገባም አሳስበዋል።



*ብፁዕ አቡነ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት*

# የአፍሪካ ክርስቲያኖችን ከጥቃት ለመከላከል ያለመ ውይይት ተካሄደ

*በካሣሁን ለምለሙ*

የአፍሪካ ክርስቲያኖች በአክራሪዎች የሚደርስባቸውን ጥቃት ለመከላከል ዓላማው ያደረገ የበይነ መረብ ቀጥታ ውይይት መደረጉን ኦርቶዶክስ ኮግኔት ፔጅ አስነብቧል።

ውይይቱ በሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክና በሩሲያ የሃይማኖት ነፃነት መከላከያ ማኅበር አነሳሽነት የተጀመረ ሲሆን በአፍሪካ የሚገኙ ክርስቲያኖችንና ቅርሶችን ከአክራሪዎች ተደጋጋሚ ጥቃት ለመከላከል የመፍትሔ አቅጣጫዎች የተቀመጡበት እንደሆነ ዘገባው አስረድቷል።

በቀጥታ ውይይቱ የተገኙት የሞስኮ መንበረ ፓትርያርክ የውጭ አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት ክፍል ኃላፊ የሆኑት ሂላሪዮን ቮሎኮላማስኬ ‹‹በአክራሪዎች ጥቃት እየተሠቃዩ ያሉ አፍሪካውያን ክርስቲያን እኅት ወንድሞቻችንን መደገፍ የሩሲያ ቤተ ክርስቲያን እንደ ታሪካዊ ተልእኮ ትቀበለዋለች›› ማለታቸውን ከዘገባው ለማወቅ ተችሏል።

የሞስኮው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ኪሪል እና ሁሉም ሩሲያዊ በግፍ ከሚገደሉትና ከሚሠቃዩት አፍሪካውያን ክርስቲያኖች ጎን እንደሚቆሙ ዘገባው ያስረዳ ሲሆን የአክራሪዎች ድርጊትም በተባበሩት መንግሥታቱ የሕግ ማዕቀፍ መሠረት መፍትሔ እንዲሰጠው እንደሚደረግም ዘገባው አስነብቧል።

ዓለም በኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ እየተፈተነች ባለችበት በዚህ ወቅት የአፍሪካ ክርስቲያኖች ግድያና ስደት ጨምሯል ያሉት ደግሞ የግብፅ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፅዕ ወቅዱስ አቡነ ታዎድሮስ ሁለተኛ ናቸው።

የኦርቶዶክስ ኮግኔት ፔጅ ሶሳይቲ የውጭ ጉዳይ ኃላፊ ፋዘር ዶክተር ያዕቆብ በበኩላቸው በኢትዮጵያ ያለው የብሔር ልዩነት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለተደጋጋሚ ጥቃት እንዳጋለጣት አንሥተው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን መደገፍ የሁሉንም ምእመናን መብት ማስከበር እንደሆነም ተናግረዋል።

በበይነ መረብ የቀጥታ ውይይቱ ወቅት የአፍሪካና የተለያዩ ዓለማት እምነት ተቋማት ተወካዮች የተሳተፉ ሲሆን ኦርቶዶክስ ኮግኔት ፔጅና ፓን ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ሶሳይቲ ላበረከቱት አስተዋጽኦ በተወያዮቹ ዕውቅና ተሰጥቷቸዋል።

# አጽዋማትንም ሆነ በዓላትን እንደ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሚከበሩ ዐበይት በዓላት ውስጥ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል አንዱ ነው። በዓሉ ከፋሲካ በዓል ቀጥሎ ከረጅም የጾም ወቅት በኋላ የሚከበር እንደመሆኑ በቤተ ክርስቲያን አባቶችም ሆነ በምእመናን ዘንድ በጉጉት የሚጠበቅ፤ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት፣ ሰፊ ዝግጅት ተደርጎበት የሚከበር ትልቅ በዓል ነው። በቤተ ክርስቲያን ከዋዜማው ጀምሮ በታላቅ ሥርዓተ ማኅሌት ተጀምሮ በሥርዓተ ቅዳሴ የሚጠናቀቅ ልዩ በዓል ነው። በምእመናንም ዘንድ ሁሉም እንደየአቅሙ በቤት ውስጥ ከሚደረገው የምግብ መጠጥ ዝግጅት ባሻገር በዓሉን በቤተ ክርስቲያን በመገኘት ከአባቶች ካህናት ጋር በመሆን በስብሐተ እግዚአብሔር የሚያከብረው ክርስቲያን ቁጥርም ቀላል አይደለም።

ይሁን እንጅ በቤተ ክርስቲያን ልዩ ቦታ እና ክብር የሚሰጠው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል ከጊዜ ወደ ጊዜ ሃይማኖታዊ መልኩን፣ መንፈሳዊ ይዘቱን እና ታሪካዊ ክብሩን በለቀቀ መልኩ መከበር ከጀመረ ዘመናትን አስቆጥሯል። እንዲህ ዓይነቱን ፈር የለቀቀ ከመንፈሳዊነትም የተፋታ የበዓል አከባበር ወደ መንፈሳዊ ይዘቱ ለመመለስ በየጊዜው በአባቶች ትምህርት ቢሰጥም በብዙዎቻችን ዘንድ በቸልታ ሲታይ ቆይቷል። በዚህ የሥርዓት መፋለስ ውስጥ ምእመናን ብቻ ሳይሆኑ አንዳንድ አባቶችም ተሳታፊ መሆናቸው ወይም ነገሩን በቸልታ ማየታቸውም የዐደባባይ ምሥጢር ከሆነ ቆይቷል።

ለምሳሌ በዓሉ ከረጅም የጾም ወቅት በኋላ የሚከበር መሆኑ ቢታወቅም አሁን አሁን ከዚህ የጾም በረከት የሚካፈል ምእመናን ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሽቆለቆለ መምጣቱን የምንታዘብባቸው ገጠመኞቻችን ብዙዎች ናቸው። ሰዎች ተገደው የማይጾሙባቸው ምክንያቶች ቢኖሩም በምናለበት የሚደረጉ እና በተለይም ‹‹የአባቶች ጾም ነው›› በሚል እና በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ በሌለ አስተምህሮ የሚጓዘው ምእመን ቁጥር ቀላል አይደለም። የቤተ ክርስቲያን አባቶች እንዲህ ዓይነቱን ከቤተ ክርስቲያናችን አስተምህሮ የወጣ ሥጋዊ አካሄድ ሲያዩ ቸል ሊሉ አይገባም።

ቀደም ባሉት ጊዜያት የአጽዋማት ወራት ሲመጡ የሚዘጉ የአጽዋማት ወቅት ሲያልቅ ደግሞ የሚከፈቱ የሥጋ መሸጫ ቤቶች ዛሬ ዛሬ በጾም ወራት ውስጥ በብዛት ተከፍተው ማየት የተለመደ ሆኗል። የእነዚህ ሥጋ ቤቶች ባለቤቶችም አብዛኞቹም ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ሆነው መገኘታቸው ለክርስትና ህይወታቸው ያላቸውን ግዴለሽነት ማሳያ ነው። የቤተ ክርስቲያን አባቶች እንዲህ ዓይነቶቹን በስም ክርስቲያን የሆኑ ምእመናንን ‹‹ለምን?›› በማለት ሊጠይቋቸው፣ ‹‹ልክ አይደለም›› በማለት ሊገስጹአቸው ትክክለኛውንም መንገድ ሊያሳዩቸው ይገባል።

በሌላ በኩል ደግሞ የጾም ወቅት በሚጀምርበትና በሚፈጸምበት ጊዜም የሚታየው አቀባበል ሌላው ከሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ያፈነገጠና ፍጹም ሥጋዊ ሆኖ ነው የሚታየው። ጾም ሲፈታ በሚጾመውም ሆነ በማይጾመው ክርስቲያን ዘንድ የሚታየው ግርግር

ከጾም ዓላማ ጋር ፈጽሞ የማይገናኝ ነው፡፡ ጾሙ ፍጹም ለሥጋዊ ፈቃድ ያደላ፣ የበዓሉ ዋና ዓላማ የተዘነጋበት ጊዜ ሆኖ ነው የሚያልፈው፡፡ አባቶች እንዲህ ዓይነቱን ሥር የሰደደ እና የቤተ ክርስቲያንን በዓላት መልክ የቀየረ አካሄድ ከዐውደ ምሕረት ትምህርት ባሻገር ለንስሐ ልጆቻቸው በተናጠልም ቤት ለቤት ሊያስተምሩ ብሎም ሊገሥጹ ይገባል፡፡

በጾም ወራት በተለይ በሚጀምርበት እና በሚፈጸምበት ጊዜ ለምግብ ለመጠጥ የሚወጣው ወጪ እና የሚከናወነው ዝግጅትም ሌላው ፍጹም ከቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ያፈነገጠ፤ የአብርሃምንም መንገድ ያልተከተለ ነው፡፡ ብዙ ችግረኞች ባሉባት ሀገራችን ተካፍሎ መብላት፣ ምንዱባንን ማሰብ ከክርስቲያኑ ልቡና ከተሰደደ ቆየ፡፡ ለራስ ብቻ የሚታሰብበት ከአቅም በላይ የሚበላበት አሁን አሁን በዓሉ ምግብ መጠጥ ብቻ የሚመስልበት ትዕይንት ማየት የተለመደ ነው፡፡ ተካፍሎ መብላት፣ ችግረኞችን ስለማሰብ በተማርንበት የቤተ ክርስቲያን መድረክ ሳይቀር መታየቱ እጅግ ያሳፍራል፡፡ መብል መጠጡ ምንም የሌላቸውን ያላሳተፈ መሆኑ የክርስትናችንን ልክና መጠን የሚያሳይ ነውና ከዚህ ዘልማዳዊ አዙሪት እንወጣ ዘንድ ሊታሰብበት ይገባል፡፡

‹‹በመጠን ኑሩ›› ተብሎ በተጻፈው አምላካዊ ቃል መሠረት በመጠን መኖርና እንደ አባቶች አስተምህሮ መመላለስ ይገባል፡፡ በዓል ሲደርስ በቤት ውስጥ ብቻ ተወስኖ በምግብና በመጠጥ ብቻ ማሳለፉ የክርስቲያን ወግ አይደለም፡፡ ብዙዎች በዓል ሲመጣ ለበዓሉ ያስፈልጋል የሚሉትን ከማዘጋጀት ውጪ በቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ሥርዓት ውስጥ ሲሳተፉ አይታዩም፡፡ ለምሳሌ ከጾም በኋላ ስለሚበላው ምግብ እንጂ ካላቸው ላይ ለድሆች ስለማካፈል አያስቡም፣ በጾም ውስጥ ስለሚዘጋጀው ምግብ እንጂ ስለጸሎት፣ ንስሐ ስለመግባት ግድ የላቸውም፤ ጾመው ስለመዋል እንጂ ስለሌሎች የትሩፋት ሥራዎችም የሚመለከታቸው አይመስልም፤ ሰዓት ጠብቆ ስለመብላት እንጂ ጊዜ ቢኖራቸውም እንኳ ማስቀደስ ትውስ አይላቸውም፡፡

ጾም ሲፈታም እንደዚያው ነው በዓሉን ቤተ ክርስቲያን በመሄድ፣ ከማኅሌቱ ከቅዳሴው በረከት ስለመካፈል የሚያስበው ምእመን ቁጥር ምን ያህል እንደሆነ መገመት አያዳግትም፡፡ ይህ ሥር የሰደደ በሽታችን ነውና በቃለ እግዚአብሔር ሊፈወስ ይገባዋል፡፡ የአብዛኛው ምእመን መልክ ይህን ይመስላልና ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ብዙዎች ከዚህ ሥጋዊ ልምድ እንዲወጡ በትጋት ልትሠራ ይገባታል፡፡ የቤተ ክርስቲያን አጽዋማትንም ሆነ በዓላትን እንደ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ልናሳልፍ ይገባል የሚለው የዛሬው መልእክታችን ነው፡፡

# የማንቂያ ደወል የሆነው የኮሚሽኑ ሪፖርት

በዲ/ን አሻግሬ አምጤ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን የአርቲስት ሐጫሉ ሁንዴሳን ግድያ ተከትሎ በኦሮምያ ክልላዊ መንግሥት የተፈጸመውን ጭፍጨፋ አስመልክቶ ባለ ፳፬ ገጽ ሪፖርት ይፋ አድርጓል:: ከኮሚሽኑ ሪፖርት መረዳት የሚቻለው የተፈጸመው ጥቃት ኦርቶዶክሳውያን ላይ ያነጣጠረ መሆኑን ነው:: ሕይወታቸውን ማጥፋት ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ጥበቃ ቢተርፉ እንኳ የሚበሉት እንዳይኖራቸው ንብረታቸውን መዝረፍ፣ ማቃጠል፣ አፈናቅሎ በማሳደድ በችግር ሲሠቃዩ እንዲኖሩ ማድረግ መሆኑን መረዳት ይቻላል:: የኮሚሽኑ ሪፖርት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስታሳስበው የከረመችውን የሚያጠናክር በአንጻሩ መንግሥት ጥቃቱ አጋጣሚ የፈጠረው እንጂ በተጠና መልኩ የተፈጸመ አይደለም በማለት ሲያስተባብል የከረመውን የሚያጋልጥ ሪፖርት ነው:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን የወጣ ጠንከር ያለ ሪፖርት መሆኑን አንብቦ መረዳት ይቻላል::

እንዲህ ዓይነት ሪፖርቶች እውነት ተዳፍና የምትቀር እነርሱም ከተጠያቂነት እንድናለን እየመሰላቸው በወንጀል ላይ ወልጀል፣ በኃጢአት ላይ ኃጢአት የሚደርቡ ወገኖች ሊደርስባቸው የሚችለውን አደጋ አስበው እጃቸውን ከጥፋት እንዲሰበስቡ ያደርጋል:: ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጥቅምት ወር ፳፻፲፫ ዓ.ም "የመንግሥት የበታች ባለሥልጣናት ለጥፋተኞች ከሚያደርጉት ከለላ እጃቸውን እንዲሰበስቡ"ያሳሰበችው በመዋቅር ክርስቲያኖች ሲገደሉ፣ ሲሳደዱ፣ ሀብት ንብረታቸው እየተዘረፈ ቀሪው ሲቃጠል ብዙዎቹ የክልሉ መንግሥት የጸጥታ አካላት ቆመው ያዩ ስለነበር ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ መከላከያ ሠራዊት እንዳይገባ ከመከልከል ጀምሮ የተሳሳተ መረጃ ይሰጡ እንደነበር የሚያሳየው ኮሚሽኑ መረጃ ባንክ ለመጠበቅ ብቻ ለግዳጅ እንዲሰማሩ መደረጉ መንግሥት የራሱን መቅር መመርመር ያለበት መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው::

አጠቃላይ ግኝቱ "ኮሚሽኑ ምርመራ ባደረገባቸው ፵ የኦሮሚያ አካባቢዎች የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ መገደል ከተሰማበት ሰኔ ፳፪ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም. ምሽት ጀምሮ ሰዎች በሰልፍ መልክ እና በቡድን ወደ ጎዳና በመውጣት፣ ጎማ በማቃጠል እና ድንጋይ ደርድሮ መንገድ በመዝጋት እንቅስቃሴዎች ከጀመሩ በኋላ ሰዎችን ማጥቃት እና ንብረት ማውደም የጀመሩ ሲሆን በማግስቱ ሰኔ ፳፫ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም. ሁኔታው ተባብሶ ቀጥሏል" በማለት ያብራራል:: መንገድ የተዘጋውም አድኑን ብለው ለሚጮኹ ክርስቲያኖች የክልሉ ልዩ ኃይልም ሆነ የክልሉ ፖሊስ አይቶ እንዳላየ በማለፍም ሆነ በአንዳንድ አካባቢዎች የጥፋቱ ተባባሪ በመሆኑ መከላከያ ደርሶ እንዳያድናቸው ነው:: የኮሚሽኑ ሪፖርት በመቀጠልም "ወደ አደባባይ/ጎዳና የወጡ ሰልፈኞች ከፍተኛ ሁከት እና ጥቃት ባስነሱባቸው አካባቢዎች በሰላም የሚኖሩ ሲቪል ሰዎች ሁከት ባስነሱ ሰዎችና ቡድኖች በየቤታቸው እና በየጎዳናው በግፍና በጭካኔ በዱላ፣ በጨቤ፣ በመጥረቢያ፣ በስለት ብረት፣ በድንጋይ እና በኤሌክትሪክ ገመድ ተደብድበው ተገድለዋል :: የአካል እና የሥነ-ልቦና ጉዳት ደርሶባቸዋል፤ ቤት እና ንብረታቸው ሆነ ተብሎ በእሳት ተቃጥሎ ወድሟል፤ በከፊልም ተዘርፏል:: በዚህም የተነሣ ሰዎች ከመኖሪያቸው ተፈናቅለዋል:: በግል ድርጅቶች፣ በመንግሥት እና በፖለቲካ ፓርቲዎች ንብረት ላይም ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል:: የጥቃቱ ባሕሪ እና መጠን እንደየአካባቢው ሁኔታ የሚለያይ ቢሆንም በአመዛኙ የክርስትና እምነት ተከታዮች በብዛት በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ጥቃቱ በአማራ ብሔር ተወላጆች ላይ ያነጣጠረ ሲሆን የእስልምና እምነት

ተከታዮች በብዛት በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ደግሞ በኦሮቶዶክስ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች ላይ ያነጣጠረ ነበር" ይላል፡፡

የቤተ ክርስቲያን መገናኛ ብዙኃንም ሆኑ ኃላፊነት የሚሰማቸው አካላት ከዚህ የተለየ አልዘገቡም፡፡ ምንም እንኳ የጥቃቱ ዒላማዎች ክርስቲያኖች የነበሩ ቢሆንም ቤተ ክርስቲያን እየደረሰባት የነበረውንና አሁንም ያልቆመውን የምትዘግበውና ዓለም እንዲያውቀው የምታደርገው ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ነው፡፡ ምክንያቱም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች በዚህ ምድር ያላቸው አገር ኢትዮጵያ በመሆኗ ሰላም እንዲሰፍን እንጂ የገደለንን እንግደለው በሚል አገሯን ሀገራቸውን አያፈርሱም፡፡ እንዲህ ዓይነት ተልእኮ ያላቸው አካላት ቢኖሩም ቤተ ክርስቲያን ግን የሰላም ሐዋርያ እንጂ የጥፋት መልእክተኛ ባለመሆኗ የተፈጸመባትን የምትገልጠው እንኳ መንግሥትም ሆነ የሚመለከታቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ለሰላም መረጋገጥ መፍትሔ እንዲሰጡ ብቻ ነው፡፡ ዓላማዋ አይደለም እንጂ እንደተፈጸመባት ጥቃት አጸፋውን ብትመልስ ሀገር እንደሀገር አትቀጥልም፡፡ ተልእኮዋ ሰማያዊ መሆኑ ቀርቶ ለኃላፊው ዓለም ይሆናል ማለት ነው፡፡

አስቀድመን እንደገለጥነው ኮሚሽኑ ሙስሊሞች በበዙባቸው አካባቢዎች ክርስቲያኖች ዓላማ ሆነዋል፡፡ የደረሰውንም "የእስልምና እምነት ተከታዮች በብዛት በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ደግሞ በኦሮቶዶክስ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች ላይ ያነጣጠረ ነበር" በማለት በማያሻማ መንገድ ገልጦታል፡፡ ይህ የኮሚሽኑ ሪፖርት ወቅት እየጠበቀና ምክንያት እየተፈጠረ ክርስቲያኖችን የመጨፍጨፍ ተልእኮው መፍትሔ እንዲበጅለት የጥሪ ደወል ነው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን መንግሥት በራሱ መዋቅር ተሰግስገው ገዝግዘው ለመጣል የሚሠሩ አባላት እንዳሉት ተገንዝቦ ጥፋተኞችን እየለየ ለሕግ ማቅረብ እንደሚኖርበትም የሚጠቁም ነው፡፡

"በወንጀል ድርጊቱ ሲሳተፉ የነበሩት ሰዎች ተግባራቸው ስልታዊ እና የተቀናጀ ወይም የሰፊ ጥቃት አካል መሆኑን በማወቅ የተሳተፉበት እንደነበር ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ሪፖርት በዝርዝር እንደ ተመለከተው በጥቃቱ በተሳተፉት ሰዎች በቡድን በመሆን የተፈጸሙት ጥቃቶች እንደ ተራ ወንጀል ብቻ የሚቆጠር ሳይሆን ጠቅላላ ድርጊቱና ውጤቱ በሰብአዊነት ላይ የተፈጸመ (crime against humanity) የግፍና ጭካኔ ወንጀል (atrocity crime) ስለመሆኑ የሚያሳዩ ናቸው" የሚለውን የኮሚሽኑን ሪፖርት ከጥቂት ወራት በፊት ከቀሲስ ሙሉቀን ብርሃኑ ጋር ካደረግነው ቃለ መጠይቅ ጋር ማገናዘብ ይቻላል፡፡ "በመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያንን እና ምእመናንን አክራሪ እስልምና እያጠቃቸው እንደሆነ ከመንግሥት አካላት ጋር መተማመን አልተቻለም ነበር፡፡ አሁን ግን ሁሉም የመንግሥት አካላት ጉዳዩን በሚገባ ተረድተውታል፡፡ ከዚህ ቀደም ቤተ ክርስቲያንና ምእመናንን በተደራጀና ተቋማዊ መልክ ባለው ሁኔታ እየተጠቁ እንደሆነ በተደጋጋሚ ለመንግሥት እናመለክት ነበር፡፡

**ምንም እንኳ የጥቃቱ ዒላማዎች ክርስቲያኖች የነበሩ ቢሆንም ቤተ ክርስቲያን እየደረሰባት የነበረውንና አሁንም ያልቆመውን የምትዘግበውና ዓለም እንዲያውቀው የምታደርገው ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ነው፡፡ ምክንያቱም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች በዚህ ምድር ያላቸው አገር ኢትዮጵያ በመሆኗ ሰላም እንዲሰፍን እንጂ የገደለንን እንግደለው በሚል አገሯን ሀገራቸውን አያፈርሱም፡፡**

ነገር ግን የመንግሥት ምላሽ ቤተ ክርስቲያን የምትጠቃው በድንገት እንጂ በተደራጀ ኃይል አይደለም የሚል ነበር፡፡ እና የተደራጀ ኃይል ቤተ ክርስቲያንን እያጠቃ መሆኑን የሚያሳዩ በርካታ መረጃዎች ነበሩን፡፡ ከማሳያዎች አንዱ ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን የሚጠቁት አብዛኛውን ጊዜ ሕዝበ ሙስሊሙ በሚበዛባቸው የኦሮሚያ አካባቢዎች መሆኑ ነው፡፡ ሌላው ማርጋገጫ ደግሞ በቅርቡ ሰኔ ፳፪ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም የአርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳን ግድያ ሽፋን በማድረግ እስልምና በሚበዛባቸው አንዳንድ የኦሮሚያ አካባቢዎች በምእመናን ሕይወትና ንብረት ላይ የተፈጸመው አሳዛኝ ጥቃት ነው፡፡

ጥቃቱ በተደጋጋሚ የሚፈጸመው በባሌ፣ በአርሲ፣ በጅማ፣ በሐረርጌና በከሚሴ ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው ጥቃቱ እየተፈጸመ ያለው በአክራሪ ሙስሊሞች መሆኑን ነው፡፡ … በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የሚኖሩ በርካታ የሸዋ ኦሮሞዎች ኦርቶዶክስ ክርስቲያን በመሆናቸው ብቻ ከሌሎች ቋንቋ ተናጋሪዎች ጋር በአሰቃቂ ሁኔታ ተገለዋል፤ ሀብት ንብረታቸው ተዘርፏል እንዲሁም ተቃጥሏል" የሚለው የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን አጥኚ ግብረ ኃይል መድቦ ለበርካታ ወራት አስጠንቶ ከደረሰበት ማጠቃለያ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ የሚያመለክተው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የጉዳዩን አሳሳቢነት ተረድታ ከመንግሥት ጋር ተባብራ በመሥራት ጥቃቱ እንዲቆም የምትችለውን ሁሉ ማድረግ የሚገባ መሆኑን ነው፡፡

እንደ ኮሚሽኑ ሪፖርት እኛም ስንዘግበው እንደ ከረምነው ጥቃቱን አሰቃቂ ያደረገው "መንግሥት የሌለ እስከሚመስል ድረስ …የጸጥታ አካላት በበላይ አካል አልታዘዝንም፣ የግለሰብ ንብረት ጠብቁ አልተባልንም፣ የምንጠብቀው የመንግሥት የልማት ተቋማትን፣ ባንኮችን እና የሃይማኖት ተቋማትን ነው" ብለው መልስ እየሰጡ ሀገር ሲጠፋ እጃቸውን አጣጥፈው ማየታቸው ነው፡፡ ከዚህ የኮሚሽኑ ሪፖርት በመነሣት ጥቃቱ ዳግም እንዳይከሠት መሥራት ከመንግሥትም፣ ከእያንዳንዳችን ከፖለቲካ ፓርቲዎችም፣ ከሃይማኖት ተቋማትም የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡

ለአንባብያን ተጨማሪ ግንዛቤ ለመፍጠር ከኮሚሽኑ ሪፖርት በመጥቀስ አሳባችንን እናጠቃል፡፡ "በሰዎች እና በንብረት ላይ ጥቃት ከመድረሱ አስቀድሞ ለመከላከል እና ጥቃቱን ለማስቀም የጸጥታ አካላት የነበራቸው ሚና ከቦታ ቦታ የተለያየ ሲሆን በተወሰኑ አካባቢዎች የጸጥታ ኃይሉ ቅድመ ዝግጅት በማድረጉ ጉዳቱን ለመከላከል፣ ለማስቆም ወይም ለመቀነስ ተችሏል ፡፡ ጥቃቱ ያነጣጠረው በከፊል በብሔር እና ሃይማኖታቸው ተለይተው የተመረጡ ሰዎችን ከየቤታቸው ለይቶ በማሳደድና በማጥቃት በከፊል ደግሞ ብሔርና ሃይማኖት ሳይለይ ሰላማዊ ነዋሪዎችን ወይም ሲቪል ሰዎችን ሆነ ብሎ በማጥቃት ነበር፤ ጥቃቱ የተፈጸመው የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ በተፈጠረው ሁከት እንደመሆኑ መጠንና በወቅቱ በማኅበራዊ ሚዲያና በተወሰኑ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ይተላለፉ ከነበሩት መልእክቶች እንዲሁም በወንጀል ድርጊቱ ይሳተፉ የነበሩ ሰዎችና ቡድኖች ያሰሟቸው ከነበሩ መፈክሮች አንጻር፤ ጥቃቱን በመፈጸም ይሳተፉ የነበሩት ሰዎች ተግባራቸው ስልታዊና የተቀናጀ ወይም የሰፊ ጥቃት አካል መሆኑን በማወቅ የተሳተፉበት እንደነበር ከነገሩ ሁኔታ ለመረዳት ይቻላል" ይላል፡፡ ኮሚሽኑ የተወሰነ አካልን መርጦ ለማጥፋት ታስቦበት የተፈጸመ መሆኑን ያረጋገጠውም ይህን ሁሉ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

✝ ✝ ✝

# “የአብነት መምህራኑ ምግባርና ሃይማኖትን እንጂ የተማሪን ሀገር ሲጠይቁ ሰምቼ አላውቅም”

*- መጋቤ ሐዲስ መምህር አባ ወልደ ጊዮርጊስ ጸጋው*



መጋቤ ሐዲስ መምህር አባ ወልደ ጊዮርጊስ ጸጋው

***የተወደዳችሁ አንባብያን በዛሬው የቤተ አብርሃም ዓምድ ዝግጅታችን የምናቀርብላችሁ በምስካዬ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም የሐዲስ ኪዳን መምህር የሆኑትን መጋቤ ሐዲስ መምህር አባ ወልደ ጊዮርጊስ ጸጋውን ነው። በአሁኑ ሰዓት በገዳሙ ጉባኤ ዘርግተው እያስተማሩ ሲሆን በመምህርነት ዘመናቸው ብዙ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትን፣ ኤጲስ ቆጶሳት፣ ጳጳሳትን እና መምህራንን አፍርተዋል። ዛሬ ያላቸውን የሕይወት ተሞክሮ እንዲያካፍሉን እንግዳ አድርገናቸዋል እነሆ።***

***ክፍል አንድ***

በመጽሐፈ ሲራክ

***ስምዐ ጽድቅ፦*** አባታችን ከእርስዎ ጋር ይህን ቃለ መጠይቅ እንድናደርግ ስለፈቀዱልን ከልብ እናመሰግናለን። የልጅነት ሕይወትዎን ይንገሩን? የት ተወለዱ? የእናትና የአባትዎ ስም ማን ይባላሉ?

***አባ ወልደ ጊዮርጊስ ፦*** አመሰግናለሁ የተወለድኩት ሐምሌ ፯ ቀን ፲፱፻፶፰ ዓ.ም ዕለቱ ዕለተ ማክሰኞ በሰሜን ጎንደር እንፍራዝ ከተማ ልዩ ስሙ ደብረ ገነት ማርያም በሚባል ቦታ ነው። እናቴ ወ/ሮ ጥሩዬ ዓለሙ አባቴ አቶ ጸጋው ተሻለ ይባላሉ።

***ስምዐ ጽድቅ ፦*** ስለ አብነት ትምህርት ቤት የተማሪነት ሕይወትዎ ይንገሩን ምን ድረስ ተማሩ?

***አባ ወልደ ጊዮርጊስ ፦*** በመጀመሪያ እስከ ፲፫ ዓመቴ ዘመናዊውን ትምህርት ነበር ስማር የቆየሁት። በኋላ ግን በጊዜው በነበረው የኢህአፓ ግርግር ዘመናዊውን ትምህርት ትቼ ወደ ሠይፍ አጥራ ማርያም በመሄድ አብነት ትምህርት ቤት ገባሁ። በዚያም ከመምህር ዳንኤል ዘንድ ዳዊትን፣ውዳሴ ማርያምን እና ዜማ ተማርኩ። ለግ ማርያም ከየኔታ መንክር ዘንድ ቅኔን ተቀኝቻለሁ፤ለሁለተኛ ጊዜ ከመምህር ጽጌ ዋረብ አርባዕቱ እንስሳ እና ቅኔን ተቀኝቻለሁ። ቅኔውን በደምብ ከተማርኩ በኋላ ወደ ጎንጅ ተመልሼ አራት ዓይና ከነበሩት ከየኔታ ብርሃነ መስቀል እርባ ቅምሩን፣ ንባብና ዜማውን እንዲሁም አቡሻኽሩን አጠናቀቅሁ። ቅዳሴ ከመምህር ገብረ አምላክ፣ ብሉያትን፣ ሐዲሳትን እና ፍትሐ ነገሥትን ደብረ ሊባኖስ ገዳም ከመምህር ገብረ ሕይወት ተምሬአለሁ።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** አባታችን ወደ ምንኵስና ሕይወት እንዴት ገቡ?

***አባ ወልደ ጊዮርጊስ፦*** ጎንድ ለተክለ ሃይማኖት በዓል በሄድኩ ጊዜ የገዳሙን አኗኗር፣ የአንድነት ሕይወታቸውን እንዲሁም የአባቶችን ትሕትና ስመለከት “እንዲህ ዓይነትም ሕይወት አለ” ብዬ ወደዚያ ህይወት ተሳብኩ። ከዚያ በፊት ገዳም

አላውቅም ነበር ለጊዜው በዓሉን አክብሬ ተመለስኩና ከአራት ወር በኋላ ተመልሼ ወደዚያ ገዳም ገባሁ። ወደ ገዳሙ ከገባሁ በኋላ ቅዳሴ እየተማርኩ፣ እያገለገልኩ፣ እየተላላኩሁ ብዙ ጊዜ ቆየሁ።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ከዚያስ ወዴት ሄዱ?

***አባ ወልደ ጊዮርጊስ፦*** በገዳሙ እያገለገልኩ በነበርኩበት ወቅት ቅዳሴውን ተምሬ ጨረስሁ ከዚያም በኋላ ቅዳሴውን አስመስክር አሉኝ ቅዳሴውን ሳስመሰክር ደብረ ዓባይ ሄድኩኝ። ከደብረ ዓባይ ስመለስ ወዲያውኑ ዝዋይ ትፈለጋለህ ተብዬ ወደ ዝዋይ ገዳም ሄድኩና ለሦስት ዓመት ያህል ቅዳሴ አስተማርኩ።

ነገር ግን እጅግ የበዛ የገዳም ፍቅር ስለነበረኝ ‹‹በአሁኑ ሰዓት ወንበር ላይ የምቀመጥበትና ሳንቲም የምቆጥርበት ዘመን አይደለም ዓይኔ ሳይፈዝ ደብረ ሊባኖስ ሄጄ መጋገር አለብኝ አለብኝ›› ብዬ ከዚያ ወጥቼ ወደ ደብረ ሊባኖስ ሄድኩ። ደብረ ሊባኖስ እንደደረስኩ ተቀበሉኝ በትርፍ ሰዓት ሰዓታት እየቆምኩ እያገለገልኩ ጋገራ ጀመርኩና እዚያ ለአንድ ወር ያህል ቆየሁ። ከወር በኋላ በጊዜው ያረፍኩባቸውና አሁን አቡነ ድሜጥሮስ የሚባሉት የያኔው ጓደኛዬ ‹‹የት እየዋልክ ነው?›› አሉኝ

‹‹ቤተ እግዚአብሔር እየጋገርኩ አልኳቸው።
‹‹ገዳም አይደል እንዴ ያደከው እንዴት ለሁለተኛ ጌዜ ትሄዳለህ?›› አሉኝ

‹‹እኔ ትንሽ በረከት ማግኘት አለብኝ ጎንድም ትንሽ ሳልጋግር ነው የመጣሁት›› አልኳቸው። እሳቸውም ‹‹የኔ ድርጎ ይበቃናል ሴት ደብር ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ ቀድሞ አባ ኃይለ ጊዮርጊስ ይባላሉ እሳቸው ሰው ስለሌላቸው እሳቸው ጋር እሑድ እሑድ እየቀደስክ መማር ነው ያለብህ ›› ብለው ወደ መጽሐፍ ቤት ይዘውኝ ሄዱ።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ደብረ ሊባኖስ ምን ያህል ጊዜ ቆዩ ከዚያስ?

***አባ ወልደ ጊዮርጊስ፦*** ደብረ ሊባኖስ መጽሐፍ ቤት በጀት ሳይሠጠኝ ለሁለት ዓመት እየቀደስኩ ተማርኩና ኋላ በጀት ተሰጠኝ አዲሳቱንም ዘልኩ። መምህሬ እንዳይቆጡኝ ደግሞ ተደብቄ ብሉያት እማር ጀመር እንደጨረስኩ በዚህ የሚያውቁኝ ሰዎች በጊዜው መምህር ብርሃነ ሥላሴ አሁን አቡነ ዲዮስቆሮስ ለምስካዬ ኅዙናን ገዳም ሚሆነው እሱ ነው እናምጣው ብለው ነገሯቸው። እኔ ከተማ ነው አልገባም ብዬ እምቢ ብዬ ነበር መምህር ብርሃነ ሥላሴ /አሁን አቡነ ዲዮስቆሮስ / አባብለው ይዘውኝ ወደ ምስካዬ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም በመምህርት መጣሁ።

ለጊዜው የተማሪ ቤት እስከሚሠራ ድረስ በዚህ ተቀመጥ ብለው መሪጌታ ረታ የሚባሉ ገዳማዊ ሰው ቢሮ አስለቀቁልኝ እዚያ ሆኜ አምስት ተማሪዎችንም እንዳስተምር ሰጡኝ። እሺ ብዬ ተቀበልኩና ተመልሼ ወደ ደብረ ሊባኖስ ሄድኩ። ወደ አዲስ አበባም ለመመለስ ፈቃደኛ ባለመሆኔ ወደ አብረንታንት ዋልድባ ሄድኩኝ። ዋልድባ አንድ ወር ቆይቼ ስመለስ ደግሞ ‹‹መጣ›› ሲባል መኪና ይዘው መጥተው በግድ በልመና ወሰዱኝ ምስካዬ ኅዙናን በአምስት ተማሪ የጀመርኩት ሰባት ከዚያ አስራ አራት እያለ አሁን ካለንበት ደርሰናል ማለት ነው።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** አባታችን በአብነት ትምህርት ቤት ህይወትዎ አብነት ሆነውኛል የሚሏቸው መምህራን ወይም ሊቃውንት ካሉ ቢነግሩን

***አባ ወልደ ጊዮርጊስ፦*** ከተማርኩባቸው መምህራን የወሰድኩት ጥሩም ደካማ ጎንም አለ። የነበርሁባቸው መምህራን በማስተማር በኩል ሁሉም ጥሩ ሊቃውንት ናቸው። የመጀመያው መምህሬ ጎንጅ ተክለ ሃይማኖት ምሥራቅ በለሳ የነበሩት የድጓ፣ የአቋቋም መምህር ናቸው። እጅግ ሲበዛ ቁም ነገረኛ እና ትጉህ መምህር ናቸው ነገር ግን በትንሽ ነገር ይበሳጫሉ። አንድ ተማሪ ሲያጠፋ ይናገራሉ፣ ይቆጣሉ። እኔ ወደ መምህርነት ከገባሁ በኋላ በተማሪ ላይ መበሳጨት ከንቱ መሆኑን ነው የተረዳሁት። ሁለተኛው መምህሬ ጎንጅ ተክለ ሃይማኖት የተማርሁባቸው የቅዳሴ መምህር ናቸው ድጓ አዋቂ፣ የአቋቋም መምህርም ናቸው። ከብቃት ደረጃም የደረሱ፣ ትግሃ ሌሊት ያላቸው ብርቱ መምህር ናቸው። እኚህ መምህር እኔ ሳውቃቸው አንድ ቀን ሲተኙ አይቻቸው አላውቅም። ሁል ጊዜ ማታ ድንገት ልጠራቸው ስሄድ ራሳቸውን ጉልበታቸው ላይ ደፍተው የተቀመጡበት ላይ ሆነው ነው የሚያንጎላጁት። የቤተ ክርስቲያን ደውል ሲደወል ወደ ጸሎት የሚሄዱ፤ ሕይወታቸው ሲደወል ከቤተ ክርስቲያን ተመልሰው ወደ ወንበር ነው። ሕይወታቸው እንዲህ ነው፤ ነገር ግን ቁጡ ናቸው። ያሁሉ ትግሃ ሌሊት፤ መንኖ ጥሪት እጅግ የሚያስደንቅ ነው። የቸገረው ሰው ሲያገኙ ያላቸውን ከመስጠት አልፎ ተርፎ ልብሳቸውን አውልቀው እስከ መስጠት የደረሱ አባት ናቸው። ስመ

እግዚአብሔር፣ የእመቤታችን ስም ከተጠራ ልብሳቸውን ወርውረው ጥለውት ይሄዳሉ እየተባለ ቤታቸው ጸበልተኛ፣ ተማሪ እንዳያስቸግራቸው እንዳይለምን ዘበኛ ያቆሙላቸው ነበረ። ያ ሁሉ ጉባኤ እያለ ግን ይበሳጫሉ።

ከእርሳቸው በኋላም የተተኩት መምህር ስራቸውን የሚያከብሩ፣ የሚወደዱ ሊቅ ናቸው፤ይሁን እንጂ ብስጩ ናቸው። የነገዋን ቤተ ክርስቲያን የሚረከብ ደቀ መዛሙርት የሚያፈሩ መምህራን ከተበሳጩ ተማሪ ደንጋጣ ስለሚሆን ዋጋ ቢስ ድካማቸው ከንቱ ነው ማለት ነው። እንደ አሁኑ ሰዓት ቢሆን ተማሪ አይከተላቸውም ነበር።

ሌላው ሁለቱ የቅኔ መምህራን ናቸው። አንደኛው የቅኔ ቤት መምህሬ የኔታ መንክር የሚባሉ የጎጃም ደግ ነበሩ፤ ዓይነ ስውር ናቸው ፤መልካም ስብእና ያላቸው፣ የማይበሳጩ፤ ሰው የማይነቁ ናቸው። ሁለተኛው በለሳ የተማርኩባቸው መምህር ጽጌ ዋረብ የሚባሉ ደግ መምህር ነበሩ፤ በጣም ሲበዛ ሰው አክባሪ ናቸው ሰውን ትክ ብለው አይተው ‹‹ይሄ ልጅ ለወደፊቱ ትልቅ ኃላፊነት ይጠብቀዋል›› ብለው የሚገምቱ ሰው ነበሩ። የቅኔ መምህራኑ ሁለቱም በጣም ደጋግ ነበሩ አብነት የምላቸው እነሱን ነው።

ከዚያ ቀጥሎ ጎንጅ ላይ የነበሩት ኔታ ብርሃነ መስቀል የሚባሉ የድጓው፣ የአቡሻኽሩ መምህር ናቸው። ያን ጊዜ ልጅነት ስለነበረ ማታ ማታ ነው አገባብ እርባ ቅምር የምማረው ዜማ ደግሞ በዐል በዐል እያየሁ ነው የምማረው። እሳቸው ደግሞ ተግተው ከማስተማር ውጪ ተማሪ ለምን ቀረ አይሉም። በጣም ይወዱኝ ነበረ ‹‹ልጄ በእግሬ ትተካለህ›› ይሉኝ ነበረ። ያን ጊዜ እኔ ቤተ እግዚአብሔር ጌሾ፣ ብቅል ስወቅጥ፣ እንጨት ስፈልጥ ውዬ ነው የምመጣ እሳቸው ደግሞ እየመጡ ‹‹የት እየዋልክ ነው?›› ብለው ይቆጣሉ። ‹‹ቤተ እግዚአብሔር እያገለገልኩ›› እላቸዋለሁ።

‹‹ተማር አላልኩህም ወይ ልጄ አንተ ሥራህ ይሄ አይደለም ገዳም እንጨት ሚፈልጥ አያጣም ቤተ ክርስቲያን የሚረከብ የለም አንተ ቤተ ክርስቲያን ትረከባለህ›› ይሉኝ ነበረ። ትልቁ አብነቴ እሳቸው ናቸው።

እሳቸው ገደል አህያ በተባለ ቦታ መጽሐፍ ቤት እያለሁ ነው የሞቱት። በሳቸው ሞት ዓመት አልቅሻለሁ። ሰው የሚለወጥ ቢሆን በሕይወት እንዲኖሩ ራሴን እለውጥላቸው ነበር። በጊዜው ‹‹ባህር ዳር የካህናት ማሰልጠኛ ኮርስ መሰልጠን አለብኝ ከዚያ ቶሎ እመለሳለሁ›› ስላቸው ‹‹አንተ አትመጣም እኔንም አታገኘኝም›› ይሉኝ ነበር ‹‹ጾመ ድጓ፣ ቅዳሴ፣ ሌላ በእጅ የተጻፈ ደግሞ የዜማ መጽሐፍ ነበረ እርሱን አስቀምጡ›› ስላቸው። ‹‹ አይ እኔን አታገኘኝም መጻሕፍትህን እቃ ቤት ታገኛቸዋለህ›› ብለውኝ ነበር። በጊዜው እመለሳለሁ ብዬ ስዋሻቸው አውቀውብኝ ስለነበር አትሂድ ብለውኝ ነበር። እኔ ግን በመሄዴ ወሰንኩ በኋላም ደብረ ሊባኖስ እንደምመነኩስ የምሰራውን ሥራ ሁሉ የወደፊት ሕይወቴን ነገሩኝ ።ከዚያ ከወጣሁ በዐሥር ዓመቴ ነው የተመለስኩት ያኔ ምክር ይመስለኝ የነበረው ሁሉ በሕይወቴ ሁሉም ነው የተፈጸመው በኋላ ሳስበው ነው የብቃት መሆኑ የገባኝ።

እኚህ አባት በፊት በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም ግቢ ገብርኤል የድጓ መምህር ነበሩ መፈንቅለ መንግሥት ሲነሳ ‹‹ከእንግዲህ ወዲህ ይህች ሀገር ሰላም የላትም፤ መማርያም የማስተማሪያም ጊዜም አይደለም ብለው›› የዘጉ አባት ነበሩ። እንግዲህ አብነት የምላቸው እሳቸውን ነው የቅኔ መምህራኑን እነዚያም ቢሆን ትግሀ ለሌሊት ማስተማር ሳይሰለቹ ጥዋት ማታ ከወንበር ገበታ መገኘት፣ ለጸሎት የማይሰለቹ ነበሩ።ይሄ ሁሉ ትጋት እያለ የሚናገሩት ትርፍ ንግግር እና ቁጣ እዚህ መጥቼ ሳየው ቅዱስ ጳውሎስ በገላ ፭፥፲፮–፳ የሥጋ ፍሬዎች ውስጥ አንዱ ቁጣ መሆኑን እና እነዚያን የሥጋ ሥራዎች የሚፈጽም አይጸድቅም ስለሚል ያ ቁጣቸውን ነው የምናየው ወይስ የትኛውን ነው እያልኩ አስብ ነበር። እንግዲህ ባንድ ቀን ቁጣ ሙሴም ደብረ ናባው ቀርቷል ዮሐንስ አፈወርቅም ቁጡ ሰው አይጸድቅም ብሏል ከዚያ ወዲህ ቁጡ መምህርማ ምን ያደርጋል የሚል ትምህርት አግኝቼበታለሁ ትጋታቸው እንዳለ ሆኖ ትርፉን ነገር ደግሞ ትርፍ ነው ብዬ ትቼዋለሁ።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** በአምስት ተማሪዎች እንደጀመሩ እና ቁጥሩ እየጨመረ እንደመጣ ነግረውናል አሁን ምን ያህል ተማሪዎች ያስተምራሉ?

***አባ ወልደ ጊዮርጊስ፦*** በአሁኑ ወቅት ወደ ፺፫ ይሆናሉ።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** የተማሪው ቁጥር በጣም ብዙ ነው ምናልባት ቁጥሩ መብዛቱ ያስቸግርዎት ይሆን? የተቸገሩበት ሁኔታ የወሰዱት መፍትሄ ይኖር ይሆን?

***አባ ወልደ ጊዮርጊስ ፦*** አሁን የሚማሩት አብዛኛዎቹ የአብነት መምህራን ናቸው። ከየደብሩ የመጡ አለቆችም አሉ። ሌሎቹ ግራ ጌታ፣ ቀኝ ጌታ በሚል ማዕረግ የዝማሬ የቅኔ የአቋቋም የድጓ መምህራን ናቸው። መጀመሪያ ዓመት የነበሩ ተማሪዎች ትንሽ ያስቸግሩ ነበረ ሰዎች አለቆቹ ሳይቀሩ ‹‹እነዚያን ሁከት የሚያነሱትን አትመርቃቸው›› ይሉኝ ነበረ። ‹‹እንዴ ይሄንማ ካላለፍኩት ለወደፊቱ በጎ ሰው አይገጥመኝም

ባለቤቱ ይሁዳን ባህሪው ሥራው አባረረው እንጂ ባለቤቱ ውጣልኝ አላለውም፡፡ እና ይሄንን ሳልፈው ነው ደግ ሰው የሚገጥመኝ›› እል ነበር፡፡ እነዚያ ካለፉ በኋላ ከዚያ ወዲያ ተማሪ አሁንም ሰይጣን እስከ ለተ ምጸት ይሰርልኝ እንጂ ኮሽ ብሎ አያውቅም አዋቂዎች ናቸው ስርዓት አክብረው ነው የሚመጡ ሁለት ሰዓት እዚህ ይደርሳሉ ውዳሴ ማርያም ጸሎት እንዳያልፋቸው ቀደም ብለው ነው የሚገኙት ከሩቅ ነው የሚመጡት ከአዲስ አበባ ዳርቻ ነው የሚመጡት አሁን አስራ አንድ ዓመት የተቀመጡም አሉ ብሉይም ተመርቀው ለጸሎተ ማርያም የማይለዩ አሉ፡፡ እንዲያው እንዲህ ስንል ምናልባት ሰይጣን ካፍ ሲወጣ እንዳይቀና እንጂ ያሉት ሁሉ አዋቂዎች ስለሆኑ በሚማሩበት ክፍል ውስጥ አንድ ሰው አልጎምጉሞ እኔን ቀና ብለው አይተውኝ አያውቁም፡፡ ይሄ የባለቤቱ ስጦታ የጉባኤው ባለቤት እንጂ የሰው አይደለም፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ቤተ ክርስቲያን እንደርስዎ ያሉ መምህራን እንዲበዙ ምን ማድረግ አለባት ብለው ይላሉ?

***አባ ወልደ ጊዮርጊስ ፦*** በእርግጥ መምህራኑ መብታቸው ሲከበር እነርሱም ስራቸውን ያከብራሉ፡፡ በአብነት ትምህርት ቤት አንዱ ችግር የልብ መከፈል ነው፡፡ ሰው እጠቀምበታለሁ ብሎ ካልያዘ ለማስተማር ካልተጠራ በመምህርነት ወንበር መቀመጥ የእግዚአብሔር ጥሪ እንጂ የትምህርት ችሎታ አይደለም ብዬ ነው እኔ የምገምተው፡፡ ግን ከቤተ ክርስቲያናችንም ከበላይ አመራርም መረዳት ያለባቸው መምህራንን እንደየሁኔታቸው ፣እንደየስሜታቸው ማስተናገድ አለባቸው፡፡ ብህትውና የሚፈልግ አለ፣ ወንበሩን ብቻ እያስተማረ ማገልገል የሚፈልግ አለ እንግዲህ ደብረ ሊባኖስም ጎንጅም ስናድግ የኛ የመምህራን ችግር መምህራን ስብሰባ አይገቡም ነገር ውስጥ አይገቡም በቃለ እግዚአብሔር እንጂ ስለሰው አስተያየት፣ ስለአመራር አስተያየት የስልጣን ጥማት የላቸውም፡፡ አገርህ የት ነው? አይሉም እኔ ያሳለፍኩአቸው መምህራኑ ሁሉም አገርህ የት ነው? አይሉም ምግባርና ሃይማኖት ብቻ ነው የሚጠይቁት እኔም ያን ስላየሁ ሀገርህ የት? ነው ብዬ ተማሪን ጠይቄ አላውቅም፡፡

እኛ ሰውን እናስተካክላለን ስንል የኛ ጠባይ ሰላማዊ ሰው ይለውጠዋል የመምህር ጠባይ እና ቤተ ክርስቲያን ለዚህ ትኩረት ብትሰጥ ባሉበት መምህራን መብታቸው ቢጠበቅላቸው እላለሁ፡፡ ማስተማር የሚወድ አለ የአደባባይ ሰው አለ፡፡ መምህራን የአደባባይ ሰው አይደሉም የነገር ሰው አይደሉም፣ የጋዜጣ ሰዎችም አይደሉም፡፡ ይሄ ነው እንግዲህ ካለፍላጎታቸውና ካለ ችሎታቸው ሲነካኩአቸው ጥለውት የሚሔዱት፡፡ የስልጣን ጥማት ካለው አደባባይ የመውጣት ፍላጎት ካለው ከወንበሩ ጋር አይሄድም፡፡ለምሳሌ ደብረ ሊባኖስም እያለን የድጓ ፣ የአቋቋም መምህራን እኔ አብሬአቸው ነበርኩ ጎረቤት ነን ምን ዓይይነት ፍላጎት እንደነበራቸው አውቅ ነበር፡፡ ከቤተ ክርስቲያን ፣ከአገልግሎት፣ ከጸሎት መልስ ሌላ ነገር ውስጥ አይገቡም፡፡ እንዲህ እኛ እንኳን ተማሪዎች አድመን ስናማክራቸው ‹‹ይሄ እኮ የጤና አይደለም ልጆቼ ይህን ተዉትና ዝም ብላችሁ ጸልዩ›› ይሉ ነበረ፡፡ እና መምህሩ እና ትምህርቱ፣ መምህሩና ተማሪው አልተገናኙም፣ መምህሩና ቦታው አልገናኝ እያለ ነው የሚያስቸግረው፡፡ የአካባቢው ሁኔታ ደግሞ ይወስነዋል፡፡

ትልቁ ርእሳችን መምህራን መብታቸው ይጠበቅላቸው ከመምህራን፣ አብነትነት ሲወጡ ደግሞ ምክር ይሠጣቸው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ምክር ትስጥ አንተን አይቶ የኋላ ልጅ ምን ይከተላል? ካንተ ምን እንጠብቃለን? ተብለው ለነሱም ምክር ያስፈልጋቸዋል ፡፡ ደግሞም እንደፍላጎታቸው መብታቸው መጠበቅ አለበት፡፡ የአባትነታቸው ጠባይ እንዳይቀየር ቤተ ክርስቲያን ክትትል ታድርግ፡፡ ብዙ ጊዜ በየቦታው የሚያጋጥም ነገር አለ፡፡ ብዙ ዘመን አገልግለው የኖሩ መምህራን አዲስ አመራር ሲመጣ የኖሩበትን የጸለዩበትን ቤት የጸለዩበትን ቦታ ልቀቁ አርጅታችኋል ይሏቸዋል፡፡ ይሄ ግፍ ሰው እንዳናወጣ ያደርገናል፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ብዙዎቹ ቀን እየሰሩ በትርፍ ሰዓታቸው ለመማር ቢያስቡ ምን ዓይነት ነገር ይመቻችላቸዋል

***አባ ወልደ ጊዮርጊስ፦*** ያው ትምህርት ቤቱ በግቢው ውስጥ ሲሆን ነው የሚመቸው እዚያ ሆነው ሲማሩ ማለት ነው፡፡ መማሩ እውቀት መጨመሩ ጥሩ ሆኖ አንድ ሰው ደግሞ ብቻውን ሆኖ የሚኖር ከሆነ የሌላው አይገባውም ከሰው ጋር መኖርን የተማሪ እና የአስተማሪ ፍላጎትን የጊዜውን ሁኔታ ያን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ግን ብዙ ጊዜ አስተማሪው የሚወጣ የሚገባ ከሆነ ተማሪውም ባካና ነው የሚሆነው፡፡ ችግሩን ስላየሁት ነው አሁን በአዲስ አበባ ያሉ ብዙዎቹ ቀን አስተምረን ማታ እንማራለን ማታ አስተምረን ቀን እንማራለን ሲሉ ተማሪው ሁሉ በዚያው ባካና ነው የሆነው፡፡ እውቀት መጨመሩ የመማር ፍላጎቱ ማዳበሩ እንዳለ ሆኖ የመምህሩ ልቦና በባከነ ቁጥር የተማሪውም እግረ ልቦና እየባከነ ነው የሚሄደው፡፡ መምህሮቻቸው በፈለጉአቸው ሰዓት ወንበር ገበታ ላይ አይገኙም ምንም ሳይጎድላቸው ማለት ነው፡፡ ለአብነት ትምህርት ቤቱ መነሻው ገጠር ነው ያ ሁሉ መምህራን ይዞሩ ነበር ወይ? ነው፡፡ የአቋቋሙም፣ የዝማሬው

መምህርም ቤተ ልሔም ብንሄድ፤ ዙራምባ ብንሄድ ፤ጎንደር ብንሄድ አጫበሩ፣ ቆሜው፣ ጎጃም ብንሄድ እነዚህ ሁሉ መምህራን በዐት ይለቃሉ ወይ? ነው፡፡ እነዚያ መምህራን ፈልሰው አዲስ አበባ ገብተዋል፡፡ ያ ተማሪያቸው ግን ከዚያ አልተተካም፡፡ ለምን እውቀት ፈላጊዎች እናተርፋለን ሲሉ እያጎደሉ መጡ በበዐት ባለመገኘታቸው እኮ ነው፡፡ ከዚያ ለምኖ ነው የሚማረው ከዚህ ግን ድርጎ አለው፤ ደሞዝ አለው፤ ግን እንዳይቀመጥ የመምህሩ ቀልብ በባከነ ቁጥር ተማሪውም ባካና ይሆናል ነው የኔ ፍርሃት መማሩ እንዳለ ሆኖ ማለት ነው፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ባገልግሎት ዘመንዎ መምህርም ከሆኑ በኋላ ተማሪም እያሉ ያጋጠሞት መልካምም ሆነ መጥፎ አጋጣሚ የሚሉት ካለ ቢገልጹልን?

***አባ ወልደ ጊዮርጊስ፦*** አንዴ አባይን ከጓደኛዬ ጋር ስንሻገር የገጠመኝ ነው ፡፡ ነሐሴ ፫/3/ ቀን በፍልሰታ በቆሎ ስንለምን ውለን ወዲህ ማዶ ቆይተን ወዲያ ማዶ ለመሻገር ታንኳ ይዘን ሳለ ማዕበል ተነሳና ተመለስን መንገድ ላይ አንድ ሰው እኔ ላሻግራችሁ አለን ዐሥር ዐሥር ሣንቲም ከፈልንና መካከል ላይ ስንደርስ ማዕበል ሞገድ ተነሳ እና እንግዲህ ለእቃው አትዘኑ ታኳው ከተገለበጠ ታንኳውን ያዙ ብሎ ያ ማዕበል መጥቶ ሲያሰጥመን ታንኳው ሳያሰጥመን ውስጥ ገብተን እንወጣለን ሰውየው ቆሞ አባይ ተወልዶ አባይ ያደገ እያለ ምንም ሳንል ብስብስ ብለን አባይ ዳር ላይ ደረሰን፡፡ ያን ተአምር ካየሁ በኋላ ‹‹ከእንግዲህ ሞት የለም›› ብያለሁ፡፡

**ሁለተኛው መምህሬ ጎንጅ ተክለ ሃይማኖት የተማርሁባቸው የቅዳሴ መምህር ናቸው ድጓ አዋቂ፣ የአቋቋም መምህርም ናቸው፡፡ ከብቃት ደረጃም የደረሱ፣ ትግሃ ሌሊት ያላቸው ብርቱ መምህር ናቸው፡፡ እኚህ መምህር እኔ ሳውቃቸው አንድ ቀን ሲተኙ አይቻቸው አላውቅም፡፡ ሁል ጊዜ ማታ ድንገት ልጠራቸው ስሄድ ራሳቸውን ጉልበታቸው ላይ ደፍተው የተቀመጡበት ላይ ሆነው ነው የሚያንጎላጁት፡፡**

***ስምዐ ጽድቅ፦*** መቼም እዚህ ለመድረስ ከእግዚአብሔር በታች አስተዋጽኦ ያደረገ አካል ሊኖር ይችላል የቤተ ሰብዎ የእናት አባትዎ አስተዋጽኦ ከዚህ በተጓዳኝ ደግሞ እዚህ ለመድረሴ ትልቅ ቦታ አላቸው የሚሏውን ከቤተሰብዎ ጀምሮ ቢነግሩን?

***አባ ወልደ ጊዮርጊስ፦*** አባቴ በትምህርት ሕይወቴ ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው፡፡ ለምሳሌ በመጀመሪያ ዲቁና ልቀበል ስሄድ ጳጳሱ ጠፉ ሁለተኛ ሂዱ ሲባል ተናድጄ አልሄድም አልኩኝ ኋላ አባቴ አታሎ ‹‹ ልጄ አይዞህ ክህነት እኮ የውስጥ ስልጣኔ ነው ረድኤተ እግዚአብሔር ይቀርብሃል አቃቤ መልአክ ያቀርባል ጤና ይሰጣል እንደው ክትባት እኮ ነው አይዞህ እንደሞግዚት አሳዳጊ ማለት እኮ ነው›› ብሎ ራሴን አሻሸቶ ‹‹አትበሳጭ እንጂ ክነት ጥሩ እኮ ነው፤ አይዞህ ለሰው ትተርፋለህ እሺ በልና ›› ብሎ ቀስ ብሎ እየጎተተ አንገቴን ታቅፎ ይዞኝ በመሄድ ዲቁና እንድቀበል አድርጓል፡፡ በኋላም የአገባብ መምህራችን ‹‹ልጄ አንተ የገዳም ሰው ነህ ስለ ዓለም እንዳታስብ›› ይሉ ነበር ፡፡ በፈቃደ እግዚአብሔር ነው ውስጡ ግን የአባቴም ፈቃድ ፈቃዱ ነው እላለሁኝ፡፡ እንድመነኩስ፣ መንፈሳዊ እንድሆን፣ ትልቅ ቦታ እንድደርስ ከዚያ በፊት ብዙ አጎቶቻችን ጥሩ ጥሩ የድጓ መምህራን ነበሩ እኔ ግን ይህን አላስብም ነበረ በፈቃዴ ወንበር ተክዬ እዚህ እደርሳለሁ ብዬ አላስብም ነበረ፡፡ እነዚህ በሕይወቴ ውስጥ ትልቅ ቦታ አላቸው፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ወላጅ አባትዎ?በቤተ ክህነት ትምህርት ትምህርቱ ነበራቸው?

***አባ ወልደ ጊዮርጊስ፦*** ፊት በልጅነቱ ዳዊት ደግሞ ነው የተወው አጎቱ የድጓ መምህር ነበሩ፡፡ ያን አስተምረውት በኋላ ላይ‹‹አንተ እርሻህን እረስ›› ብለው ወደ እርሻ እንዲመለስ አደረጉት ምን እንደታያቸው አላወቅም፡፡ አባቴ ጥሩ አራሽ አምራች ገበሬ የነበረ፡፡ መጀመሪያ ግን ዳዊት ደግሞ ነው የተወው፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፦*** አባታችን ስለሰጡን ቃለ መጠይቅ በእግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን እግዚአብሔር የአገልግሎት ዘመንዎን ይባርክ እግዚአብሔር ያቆይልን እግዚአብሔር ያክብርልን?

***አባ ወልደ ጊዮርጊስ፦*** እኔም አመሰግናለሁ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ተከታትሎ የት ወደቃችሁ ብሎ ያንዱን ሕይወት የሰው ኑሮ አይቶ እንዲረዳ ለትውልድ የሚተላለፍ በማድረጋችሁ አመሰግናለሁ፡፡ አሁንም ክትትላችሁ ይቀጥል እላለሁ፡፡

# “የቤተ ክርስቲያኒቱን ችግር በዘላቂነት መፍታት ካልተቻለ የነገዋን ቤተ ክርስቲያን ላናገኝ እንችላለን”

*- ሊቀ ኅሩያን ቀሲስ ደረጄ ብርሃኑ*

**በእህተ ሚካኤል**

## ክፍል አንድ

***ሰኔ ወር ፳፻፲፪ ዓ.ም ከአርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳ ግድያ ጋር ተያይዞ በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች በተለይም በአንዳንድ የኦሮሚያ አካባቢዎች ላይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ በአገልጋይ ካህናት እና በምእመናን ላይ ያነጣጠረ ጥቃት ሲፈጸም ቆይቷል። የተቀናጀ እና በእቅድ የተመራ ምእመናንን፣ አገልጋይ ካህናትንና ቤተ ክርስቲያንን በእጅጉ የጎዳ የጥፋት ዘመቻ በመካሄዱ ሰኔ ወርን አነሳን እንጂ ቤተ ክርስቲያንን ዒላማ ያደረገ ጥፋት ከተጀመረ ሰነበተ።***

***በተለይ የመንግሥት ለውጥ ከተደረገ በኋላ እዚህም እዚያም ይነሱ የነበሩ የጥፋት ቡድኖች በቅድሚያ መዳፋቸውን የሚያሳርፉት በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ላይ ነው። ከነዚህ የጥቃት ዒላማ ከነበሩት ሀገረ ስብከቶች ውስጥ ደግሞ አንዱ የምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ነው። በወቅቱ በሀገረ ስብከቱ የተፈጸመውን ቤተ ክርስቲያን፣ አገልጋይ ካህናትና ምእመናን ተኮር የጥፋት ዘመቻ እና በሌሎች የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ላይ የሀገረ ስብከቱን ሥራ አስኪያጅ አነጋግረን እንደሚከተለው አቅርበናል ይከታተሉን።***

***ስምዐ ጽድቅ፡*** በቅድሚያ ሙሉ ስምዎትን ከየት እንደመጡና የአገልግሎት ድርሻዎትን ቢገልፁልን?

***ሊቀ ኅሩያን ቀሲስ ደረጄ ብርሃኑ፡*** ስሜ ሊቀ ኅሩያን ቀሲስ ደረጄ ብርሃኑ ይባላል። የምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ነኝ።



*ሊቀ ኅሩያን ቀሲስ ደረጄ ብርሃኑ*
*ምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ*

***ስምዐ ጽድቅ፡*** በአሁኑ ሰዓት በምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ያለው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ምን ይመስላል?

***ሊቀ ኅሩያን ቀሲስ ደረጄ፡*** በሀገረ ስብከታችን መንፈሳዊ አገልግሎት ወይም እንቅስቃሴ በተገቢው ሁኔታ እየተካሔደ ነው። ሥርዓተ ቅዳሴው፣ሥርዓተ ማኅሌቱ፣ የስብከተ ወንጌል አገልግሎቱ ከርእሰ ከተማው ጀምሮ በየወረዳው ባሉት አብያተ ክርስቲያናት እየተከናወነ ነው። በሰንበት ትምህርት ቤቱም አደረጃጀት ሆነ በስብከተ ወንጌሉ

ጥሩ የሆነ እንቅስቃሴ አለ፡፡ ከተወሰኑት እና አንዳንድ ከፍተኛ ችግር ካለባቸው ወረዳና አጥቢያ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት በስተቀር በአብዛኛው አገልግሎቱ በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** የሀገረ ስብከቱን አመሠራረት ታሪክ ይንገሩን?

***ሊቀ ኅሩያን ቀሲስ ደረጀ፡-*** የምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት በ፲፱፻፹፩ ዓ.ም የተቋቋመ ነው፡፡ ከዚያ በፊት ጨርጨር፣ አዳልና ጋራ ጉራቻ በሚል የሚጠራና በሐረር ጠቅላይ ግዛት ሥር ሆኖ በአውራጃ ቤተ ክህነት ነበረ የሚመራው፡፡ በኋላ ላይ በዞን ደረጃ ሲዋቀር በወቅቱ በደርግ ዘመነ መንግሥት የዞኑ አስተዳዳሪ የነበሩት አቶ ኢብራሂም ሀጂ የሚባሉ የሙስሊም እምነት ተከታይ ዞን እንደመሆኑ መጠን ለክርስትናው እምነትም የሃይማኖት አባት፤ የሃይማኖት መሪ ያስፈልገዋል ብለው መጀመሪያ ሊቀ ጳጳስ እንዲመደብ አስደርገዋል፡፡

**ምእመናን ከሌሉ ቤተ ክርስቲያን ይዘጋል። ለማን ነው የሚቀደሰው? መባውን፣ስጦታውን በመስጠት ቤተ ክርስቲያን እንዲከፈት የሚያደርጉት ምእመናን ናቸው። ቤተ ክርስቲያን እንዳትዘጋ ምእመናን ሊኖሩ ይገባል። ምእመናን ከሌሉ ካህኑም አይኖርም። ስለዚህ ካህኑም እንዳይፈልስ መሠራት ያለባቸውን ነገሮች አጠናክሮ መሠራት ያስፈልጋል።**

በዚህ መሠረት ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ የሀገረ ስብከታችን ሲዋቀር ሊቀ ጳጳስ ሆነው ተመደቡልን፡፡ በሰዓቱ ብፁዕነታቸው እኒህን የዞን አስተዳዳሪ « ኢብራሂም አይደለም ከዚህ በኋላ አብርሃም ብዬ ነው የምጠራው » ብለዋቸዋል፡፡ ከዛሬ ፴፪ ዓመት ጀምሮ በሀገረ ስብከት ደረጃ ተቋቁሞ እና ተዋቅሮ ሥራውን እየሠራ ነው ያለው፡፡ የክርስትናው እንቅስቃሴ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከዕለት ወደ ዕለት እያደገ ፤ አብያተ ክርስቲያናትም እየተስፋፉ መጥተዋል፡፡ አሁን በቅርብ ከዐሥር በላይ አብያተ ክርስቲያናት እንዲተከሉ አድርገናል፡፡ ጥሩ እንቅስቃሴ ላይ ነው ያለው፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት በተጀመረው ዘመቻ የጥፋት ዒላማ ከነበሩት አካባቢዎች አንዱ የምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ነውና እስኪ ስለዚህ ቢነግሩን?

***ሊቀ ኅሩያን ቀሲስ ደረጀ፡-*** ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለውጡን ተከትሎ በነበረው ጥፋት ከተጎዱት ሀገረ ስብከቶች አንዱ የኛ ሀገረ ስብከት ነው፡፡ በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ ጉዳት ደርሶብናል፤ ምእመናን መከራ ተቀብለዋል፤ ተሠውተዋል በጭሮ ከተማ አቶ ብርሃኑ ዝቅአርጋቸው የሚባሉ የቤተ ክርስቲያናችን ምእመን ሰማዕትነት ተቀብለዋል፡፡

በአሰቦት ከተማ ደግሞ አቶ ተድላ ከተማ የተባሉ ለቤተ ክርስቲያን ብዙ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ፤ አካባቢውን እና ቤተ ክርስቲያንን ሲደግፉ የነበሩ ምእመን ተገድለዋል፡፡ ሰኔ ፳፫ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም የአርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳን ግድያ ተከትሎ በተነሳው ሁከት ነው ሕይወታቸው ያለፈው፡፡ ሌላም የተጎዱ፣የጥቃቱ ሰለባ የሆኑ ብዙ ምእመናን አሉ፡፡ በዚያው አካባቢ ከ፳፩ በላይ ቤቶች ተቃጥለዋል ፤ ከ፲፰ በላይ ሰዎች ተደብድበዋል፤ ከ፹፬ በላይ የተለያዩ ንብረቶች ወድመዋል ጉዳት ደርሶባቸዋል፤ ከ፳፻፰ በላይ የሆኑ ምእመናን በወቅቱ ከቀዬአቸው ተፈናቅለዋል፡፡ በአጠቃላይ ምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት የጥቃቱ ሰለባ ነበረ፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** የደረሰው ጥቃት በቤተ ክርስቲያኒቱ ብሎም

በሀገር ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ እንዴት ይገልጹታል?

***ሊቀ ኅሩያን ቀሲስ ደረጀ፦*** በመጀመሪያ በዚህ ጥቃት የተነሣ ምእመናኑ ተስፋ እየቆረጡ ነው ‹‹ዛሬ ባላሰብንበት እንዲህ ዓይነት ጥቃት ከደረሰ ነገ የመኖር ተስፋችን፣ ዋስትናችን ምንድነው?›› በሚል ከፍተኛ ስጋት ውስጥ ነው ያሉት፡፡ እውነት ለመናገር ክርስቲያኑ ከፍተኛ ስጋት ውስጥ ወድቆአል፡፡ እውነት ነው በዚህ ምክንያት አንዳንዶች አካባቢያቸውን እየለቀቁ ወደ ሰፊ ከተማ፣ ወደ ትልልቅ ከተማ፣ ወደ ቤተ ሰቦቻቸው እየሔዱ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያናችን ትልቅ ጉዳት ነው፤ ትልቅም ኪሳራ ነው፡፡

እንደ ሀገርም ስናይ ከፍተኛ ባለሀብት እና ከሰሩት ሥራ ላይ ለመንግሥትም ከፍተኛ ግብር የሚከፍሉ፤ በኢኮኖሚም ከተማውን የሚያንቀሳቅሱ፤ በሥራቸውም ብዙ ሠራተኞች ያስተዳድሩ የነበሩ ምእመናን ቦታውን ለቀው ከሄዱ እንደ ሀገርም ከተማዋ ትጎዳለች፤ እየተዳከመች ትመጣለች፡፡ ቅድም እንዳልኩት እንደ ቤተ ክርስቲያን በእነሱ መሄድ ሌላውም ተስፋ እየቆረጠ ለመሄድ ልቡ ይነሳሳል፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ከዚህ በመነሣት የነገዋን ቤተ ክርስቲያን ዕጣ ፈንታ እንዴት ይገልጡታል?

***ሊቀ ኅሩያን ቀሲስ ደረጀ፦*** ሁኔታው በዚሁ ከቀጠለ ለቤተ ክርስቲያን አስጊ ነው የሚሆነው፡፡ ምክንያቱም ምእመናን ከሌሉ አገልግሎቱ ለማን ይሰጣል? ቅዳሴው፣ ስብከቱ፣ መንፈሳዊ አገልግሎቶቹ ሁሉ ለማን ነው? ለምእመን ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ባለችበት ቦታ ምእመናን፤ ምእመናን ባሉበት ቦታ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን አለች፡፡ ስለዚህ ምእመናኑ እየፈለሱ ጥለው እንዳይሄዱ የማጽናት ሥራ ያስፈልጋል፡፡

የነዋ ቤተ ክርስቲያን የተሻለ ነፃነት እንዲኖራት ፣ ምእመኑ በተሻለ ሁኔታ እና በነፃነት እምነቱን እንዲያራምድ ዛሬ ላይ ቆም ብሎ ትላንት ያልሠራናቸው ሥራዎች ምንድናቸው? ክፍተታችን ምንድነው? ነገስ ምን ማድረግ አለብን? የሚለውን ቆም ብሎ በማሰብ ሁሉም ሥራውን በአግባቡ ሊወጣ ይገባል የሚል ሐሳብ ነው ያለኝ፡፡ ስለዚህ ተግተን ካልሠራን የነገዋ ቤተ ክርስቲያን ዕጣ ፈንታዋ መዘጋት ነው የሚሆነው ማለት ነው፡፡

ምእመናን ከሌሉ ቤተ ክርስቲያን ይዘጋል፡፡ ለማን ነው የሚቀደሰው? መባውን፣ ስጦታውን በመስጠት ቤተ ክርስቲያን እንዲከፈት የሚያደርጉት ምእመናን ናቸው፡፡ ቤተ ክርስቲያን እንዳትዘጋ ምእመናን ሊኖሩ ይገባል፡፡ ምእመናን ከሌሉ ካህኑም አይኖርም፡፡ ስለዚህ ካህኑም እንዳይፈልስ መሠራት ያለባቸውን ነገሮች አጠናክሮ መሠራት ያስፈልጋል፡፡ ክፍተታችንን ካልሞላን ከባድ ነው የሚሆነው፤ እንደቤተ ክርስቲያን መሥራት ያለብንን ቤተ ክርስቲያን መሥራት አለባት እንደ መንግሥትም ደግሞ ከመንግሥት ጋር ተቀራርቦ ችግሮች እንዲፈቱ የማሳመን ሥራ መሥራት ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ይጠበቃል፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ከምእመኑ ጀምሮ እስከ ካህኑ እንዲሁም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ላይ ዘርፈ ብዙ ጉዳት ደርሷል፤ የጉዳቱ መጠን፣ በጥቃቱ ሳቢያ ከቀዬአቸው የተፈናቀሉ ምእመናንና ካህናት ቁጥር በሀገረ ስብከቱ ደረጃ የተጠናከረ መረጃ አላችሁ? ከዚህ ጋር ተያይዞ አሁን በቦታው ያሉና የተረፉ ክርስቲያኖችን የማጽናቱ ሥራ፣ በሀገረ ስብከት ደረጃ እንዴት እየተሠራ ነው?

***ሊቀ ኅሩያን ቀሲስ ደረጀ ፦*** ጥቃት የደረሰባቸውን ወገኖች በተመለከተ የተደራጀ ሙሉ ዳታ አለን በወቅቱም ለቅዱስ ሲኖዶስ ለቅዱስነታቸው ለብፁዕ አቡነ ማትያስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት አስተላልፈናል፤ ለመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤቱ ፣አዲስ አበባ ለተቋቋመው ዐቢይ ኮሚቴ በአድራሻ በደብዳቤ አሳውቀናል፡፡ ይህን ያህል ሰው ተፈናቀለ፣ ይህን ያህል ሰው ተጎዳ የሚለውን አካተን በዝርዝር አሳውቀናል፡፡ የተጎዱትን ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ልጆቿን የመፈለግ የመሰብሰብ ኀላፊነት አለባትና

በዚህም መሠረት መልሰን እንድናቋቁማቸው፣ ድጋፍ እንዲደረግላቸው ባቀረብነው መሠረት ለእያንዳንዳቸው ቡክ ወጥቶላቸው እንዲረዱ ጥረት እያደረግን ነው።

**እግዚአብሔር ይመስገን ጥቃቱ ከዚህ የበለጠ ሊሆን ይችል ነበረ፤ ከመንግሥት ጋር ተቀራርቦ በመሥራት ነው ከዚህ የከፋ ጉዳት እንዳያደርስ እና በቁጥጥር ሥር እንዲውል የተቻለው። አሁንም ካሉት የመንግሥት አካላት ጋር አብረን እየሠራን ነው። ችግሩ እልባት እንዲያገኝ አብረን ተቀራርበን እየሠራን ነው። ምእመናኑም ተስፋ እንዳይቆርጡ ጎን ለጎን የማጽናናቱን ሥራ እያከናወንን ነው።**

ይህ ጥቃት የደረሰው በሰኔ ፳፫ ብቻ አይደለም ለምሳሌ ኅዳር ፳፬ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም በመሰላ ወረዳ ዕርቀ ሰላም ሞገስ የምትባል መምህርት የ፲፭ ቀን አራስ የቤተ ክርስቲያኒቱ አማኝ የሆነች ሴት በግፍ በድንጋይ ተወግራ ተገድላለች። እዚያው ወረዳ ላይ ከ፺፭ በላይ ቤቶች ተቃጥለዋል። ሁለት ከብቶች በቁማቸው ተቃጥለዋል። አትክልቶች ተጨፍጭፈዋል እንዲሁ ኅዳር ፫ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም በደበሶ፣ በሂርና፣ በዶባ ፣በቀራሮ ጊዮርጊስ፣ በበዴሳ፣ በመጣቀሻ በተለያዩ ዞኖች ውስጥ ባሉት ወረዳዎች ተመሳሳይ ጥቃት ደርሶባቸዋል። እንዲህ ዓይነቱ ጥቃት ከዕለት ወደ ዕለት እየተባባሰ የመጣ ነበረ። በተለይ በ፳፻፲፪ ዓ.ም በሀገረ ስብከታችን የነበረው እና ያሳለፍነው ፈተና ከባድ ነው።

እነዚህን የደረሱትን ፈተናዎች መልሶ እንዳይደገሙ፤ ጥቃቶች እንዲቆሙ ከመንግሥትም ጋር ተቀራርቦ በመነጋገር፣ በማስረዳት በጽሑፍም ሪፖርት አድርገናል፤ በአካልም ቀርበን አስረድተናል። ከእግዚአብሔር በታች ሕዝቡ መንግሥትን ተስፋ አድርጎ ነው የተቀመጠው፤መንግሥት ይጠብቀኛል እያለ ነው። እግዚአብሔር ይመስገን ጥቃቱ ከዚህ የበለጠ ሊሆን ይችል ነበረ፤ ከመንግሥት ጋር ተቀራርቦ በመሥራት ነው ከዚህ የከፋ ጉዳት እንዳያደርስ እና በቁጥጥር ሥር እንዲውል የተቻለው። አሁንም ካሉት የመንግሥት አካላት ጋር አብረን እየሠራን ነው። ችግሩ እልባት እንዲያገኝ አብረን ተቀራርበን እየሠራን ነው። ምእመናኑም ተስፋ እንዳይቆርጡ ጎን ለጎን የማጽናናቱን ሥራ እያከናወንን ነው።

በሀገረ ስብከታችን ሊቀ ጳጳስ በብፁዕ አቡነ እንጦንስ የሚመራ ቡድን ከሀገረ ስብከቱ ልዩ ልዩ ኀላፊዎች፣ ከደብሩ ሰበካ ጉባኤ እንዲሁም ከምእመናን፣ከአዲስ አበባው ዐቢይ ኮሚቴ የተውጣጡ ልኡካን አንድ ላይ ተቀናጅተው በሚኤሶ፣ በጭሮ፣ በአሰቦት ቦታው ድረስ በመሄድ ተጎጂዎቹን አሰባስበን አነጋግረን አጽናንተናቸው መጥተናል። ከዚህም በተጨማሪ በጎ አድራጊዎችን በማስተባበር እና ከማኅበረ ቅዱሳን አባላት ጋር በመቀናጀት ፣ቤታቸው ድረስ በመሄድ ቁሳቁሶችን በመስጠት፣የገንዘብ ድጋፍም አድርገንላቸዋል። አሁንም በዚሁ ላይ እየሠራን ነው፤ወደ ፊትም ይህንኑ አጠናክረን እንቀጥልበታለን።

# የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት

**በቀሲስ ዘክርስቶስ ፀጋዬ**



ተወዳጅ የሆናችሁ የእግዚአብሔር ልጆች! እንደምን ከርማችኋል? በእግዚአብሔር ጥበቃ በሰላምና በጤና እንደቆያችሁን ተስፋ እናደርጋለን፤ በቤታችሁ ሆናችሁ ትምህርታችሁን በንቃት እየተከታተላችሁ ነው? በጣም ጎበዞች! በመንፈሳዊም በሥጋዊም ዕውቀት ማደግ ይኖርባችኋልና በርቱ!

ልጆች! ዛሬ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የልደት ታሪክ ይዘልላችሁ ቀርበናልና ተከታተሉን!

አውግስጦስ ቄሳር የተባለ ንጉሥ በነገሠበት ዘመን በግዛቱ ያሉ ሕዘቦቹን ለማወቅ በእስራኤል ሀገር ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች በሙሉ ይቆጠር ዘንድ አዘዘ፡፡ በትእዛዙ መሠረትም ሰው ሁሉ ሊቆጠር ወደ የትውልድ ከተማው ሄደ፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም በዚያን ወቅት ጌታችንን አርግዛ ስለነበር ከአረጋዊው ዮሴፍ ጋር ሆና ለመቆጠር ከናዝሬት ወደ ትውልድ ሥፍራቸው ቤተ ልሔም ሄዱ፡፡ በቤተ ልሔም ሳሉም እመቤታችን ማርያም የምትወልድበት ቀን ደረሰ፡፡ በዚያ ሥፍራም ብዙ ሰው ስለነበር እነ ዮሴፍ የሚያርፉበት ቦታ አላገኙም፡፡ ማደርያም ስላልነበራቸው በከብቶች በረት ውስጥ ዐርፈው ሳለ እመቤታችን የመውለጃዋ ጊዜ በመድረሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ወለደችው፡፡ በጨርቅ ጠቅልላ እዛው በበረት ውስጥ አስተኛችው፤

በዚያ ሀገር ይኖሩ የነበሩ እረኞችም ሌሊት ከብቶቻቸውን ይጠብቁ ነበር፤ የእግዚአብሔር መልአክም በእረኞቹ አጠገብ ቆመ፤ የእግዚአብሔርም ብርሃን በዙሪያቸው በራ፤ በጣምም ፈሩ፡፡ መልአኩም እንዲህ አላቸው ‹‹እነሆ ለእናንተና ለሕዝቡ ሁሉ ደስታ የሚሆን ታላቅ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ፤ እነሆ፥ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኀን ተወልዶላችኋል፡፡ ይኸውም ጌታ እና እግዚአብሔር የሆነ መድኃኒታችን ኢያሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እናንተም ባገኛችሁት ጊዜ ምልክቱ እንዲህ ነው፡፡ ሕፃን በጨርቅ ተጠቅልሎ በበረት ውስጥ ተኝቶ ታገኙታላችሁ፤ ድንገትም ከዚያ መልአክ ጋር ብዙ የሰማይ መላእክት እግዚአብሔርን እያመሰገኑ መጡ፡፡›› (ሉቃ.፪÷፲-፲፫)

ከዚህም በኋላ እነዚህ እረኞች እርስ በርሳቸው ‹‹እስከ ቤተ ልሔም እንሂድ፤ እግዚአብሔርም የገለጠልንን ይህን ነገር እንወቅ›› አሉ፤ ፈጥነውም ሄዱ፡፡ ድንግል ማርያምንና ዮሴፍንም በከብቶቹ በረት አገኙአቸው፡፡ ሕፃኑንም በአዩት ጊዜ የነገሩአቸው እውን መሆኑን ስላዩ በጣም ተደነቁ፡፡ እረኞቹም እንደነገሩአቸው ባዩትና በሰሙት ሁሉ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ‹‹በሰማይ ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን፤ በምድርም ለሰው ልጆች በጎፈቃድ ሆነ›› ብለው እያመሰገኑና እያከበሩ ወደመጡበት ተመለሱ፡፡ ሰብአ ሰገልም በኮከብ ተመርተው ወደ ሕፃኑ ገብተው አምላክነቱን በመረዳት ሰገዱለት፤ ዕጣን፣ ወርቅና ከርቤንም የእጅ መንሻ አድርገው አቀረቡለት፡፡ (ሉቃ.፪÷፲፭-፲፰)

ልጆች! እነዚህ ጌታችን መድኃታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሊያዩ የመጡ ሰዎች በደስታ የጌታችንን መወለድ አክብረዋል፡፡ ስለዚህ እናንተም በቤተ ክርስቲያን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ልደት በደስታ ልታከብሩ ይገባል፡፡ አንድ ላይም ‹‹በሰማይ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን›› እያልን እንዘምር፤ እንግዲህ ለዛሬ በዚህ ይብቃን፤ ልጆች! መልካም በዓል እንዲሆንላችሁ እንመኝላችኋለን!፡፡ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ምልጃ፤ የሰብአ ሰገሉ ረድኤት አይለያችሁ!

# የዝክራችን መልክ

ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ

ዝክር አንድን ቅዱስ የተወለደበትን፣ ያረፈበትን፣ ተአምራት የሠራበትን፣ መከራ የተቀበለበትን የክብር አክሊል የተቀዳጀበትን….ወዘተ በመሰባሰብ ወይም በተናጠል ማሰብ ማለት ነው። ኦርዶክሳውያን ቅዱሱን ከማሰብ ጀምሮ፣ በጸሎትና ምስጋና እንዲሁም በቅዳሴና በውዳሴ ይዘክሩታል። በቅዱሱ ስም ከሚጠራ ሩቅ ወይም ቅርብ ቤተ ክርስቲያን ወይም ገዳም ሄዶ በመሳለምም ይዘክራሉ። ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ውሃ ከማጠጣት፣ ቆሎ ከማዘገን ጀምሮ ሰፋ ያለ ድግስ ደግሶ ነድያንን፣ ጎረቤትን ወዳጆችን ጠርቶ ‹‹ብሉልኝ ጠጡልኝ›› በማለትም ይዘክራሉ።…..

ዛሬ ዛሬ ግን ነባሩን የዝክር መልክ የቀየሩ ክዋኔዎች እየመጡ ነው። በቅዱሱ/በቅድስቷ ስም ተጠራርተው ባልተቀደሱ መንገዶች እየሄዱ ብቻቸውን አብዝተው እየበሉ እየጠጡ ዝክር እንዳደረጉ የሚያስቡ ሰዎች አሉ። ቆርሰው ለድሆች የማያጎርሱበት፣ ቀድተው ለምስኪናኖች የማያጠጡበት ዝክር በርክቷል። ጥቂቶች ከመንደር ተጠራርተው ዛሬ ቅዱስ ‹‹እገሌ›› ነው ብለው በልተው ጠጥተው ከመለያየት በስተቀር ስመ አምላክ ሳይጠራ፣ ስለቅዱሱም ሳይወራ፣ ጸሎት ሳይደረግ፣ ሳይመሰገን በመብል ተጀምሮ በመብል የሚያልቅ ዝክር አለ። ለእነዚህ ወገኖች ዋናው አጀንዳ ተሰብስቦ መብላት ብቻ ነው።

ተሰብስበው በልተው ከመለያየት ተሻግሮ ደግሞ በዝክር ስም በተደረገው ሰብሰባ የባጥ የቆጡን ማውራት፣ በሐሜት መሙላት፣ በሌላው ላይ በመፍረድ መሰልጠን ይታይበታል። በዚሁ አጋጣሚ ተከራክረው ተካረው፣ ክፉ ደግ ተነጋግረውም የሚወጡ ይኖራሉ። ማን ምን አለ? ብለው ታዝበው ከሚወጡት ጀምሮ ‹‹ለካ እገሌ እንደዚህ ዓይነት ሰው ነው›› ብለው ቂም የሚይዙ፣ የሚያኮርፉም ይኖራሉ።

ሌላው አስከፊ ገጽታ ደግሞ ዝክር ብለው ጠርተው የዘፈን ድግስ ሲያቀርቡም የሚታዩ አሉ። ዘፈን እያማረጡ በጂፓስ በታዳሚው ጆሮ ሲያፈሱ የሚቆዩ ይታያሉ፤ የቴሌቪዥን ስክሪኖቻውም ተመሳሳይ ትዕይቶችን በማሳየት ስለሚቆዩ ለአፍታም ክርስያናዊ ዝክር ሳይመስላቸው ‹‹ያክብርልን›› ብለው የሚወጡ ሰዎች ብዙ ናቸው። ከከንቱ ድምፅና ምስል አጀቡ በተጨማሪ ተንቀሳቃሽ ስልኮቻቸውን አውጥተው በመጎርጎር በፌስቡክና በቴሌግራም የተለቀቁ ልዩ ልዩ ዓለማዊ ጉዳዮችን እያዩና እያሳዩ የተ ገቡተው እንደወጡ እንኳን እስከማያስታውሱት ድረስ አእምሯቸውን አባክነው የሚለያዩም የዝክር ተሳታፊዎች በርካቶች ናቸው። በዝክሮቻቸው ነዳያን ብቻ ሳይሆን የካህን ዘር የማይገኝበት ኦርቶዶክሳዊ ለመሆኑ ምስክር የሚሆኑ ምልክቶች የማይታይበትም ዝክር ያጋጥማል።

ሌላው ዝክር ደግሞ ከቤተ ዘመድ ጉባኤ ያልተለየ ሆኖ ሊታይ ይችላል። ከቤተ ዘመዱ ያልተሻገረ፣ ቤተሰባዊ ወግ ናኝቶበት የሚውል ስመ ዝክርም አልፎ አልፎ እናገኛለን። አስገራሚው ከዚህ ሰፋሁ ብሎ ቢገኝ በቋንቋ ወይም በትውልድ ሀገር ተመራርጦ የጎጥ ዕድር የሚመስል ዝክርም እናገኛለን። በዚህ ዓይነት ቤተሰባዊ እና ጎጠኛ ስመ ዝክር ውስጥ የሚጠሩበትን የወገን መስፈርት ብቻ በመመልከት የሚታደሙ

መናፍቃን የቤተዘመዱ አባላትና የጎጥ ስብስቦችም ስለሚያጋጥሙ ለክርስቲያን ግራ ሊያጋባ ይችላል፡፡

በጥቅል ሲታይ አጉል የሆነው የዝክር መልክ አጉል ያሰኘውን መልክ የሚላበሰው በዝክሩ ዘካሪዎች ብቻ ሳይሆን በዝክሩም ተሳታፊዎች መሆኑን ማስተዋል እንችላለን፡፡

ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ ዝክርን ከዓላማው ጋር የሚያስማሙ ከመስመር ሳይወጡ የሚፈጽሙ አሉ፡፡ ቃለ እግዚአብሔርን በድምፅ ወይም በድምፅ ወምስል እያቀረቡ ሰዎችን በዚያ አጋጣሚ ወደ እግዚአብሔር ቃል የሚያቀርቡ ምስጉኖች አሉ፡፡ መዝሙሮችን በማሰማት የሰዎችን መንፈስ ወደ መንፈሳዊው ዓለም የሚስቡ ለንስሓ የሚያነቃቁ፣ለበጎ ቅናት የሚያደርሱ ብዙዎች ናቸው፡፡

**በአጠቃላይ ሲታይም አሁን አሁን የሚታየው አጓጉል የሆነው የዝክር አዘካከር በየጊዜው እየተፈታተነን ያለው ዓላማዊነት ምን ያህል እየሸረሸረን መሆኑን የምናስተውልበት ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ደግሞ ፍጹም መንፈሳዊ መልክ ለማስያዝ የሚተጉ በርካታ ክርስቲያኖች ሲታዩ ደግሞ ተስፋ እንዳንቆርጥ የሚያደርግ የመልካሙ ዝክር መልክ እንዳይለወጥ አብነት የሚያስቀርልን ሆኖ እናገኘዋለን፡፡**

በዝክሮቻቸው አጋጣሚ የአካባቢዎቻችን ችግረኞች እንዴት አድርገው እንደሚረዱ፣ ለዚያ የሚያገለግል ማኅበር ስለማቋቋም የሚመክሩ አሉ፡፡ በአካባቢያቸው ያሉ የአእምሮ ሕሙማንን፣ ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናትን፣ ጧሪ የሌላቸው አረጋውያንን የሚደግፉ ለችግረኞች ርዳታ የሚያደርጉ ድርጅቶችን ስለማቋቋም የሚመክሩ አሉ፡፡ በሌላም በዕለቱ ስሙ በሚጠራው ቅዱስ ስም ያለ አጥቢያን ስለመደገፍ፣ የጎደለውን ስለማሟላት የሚነጋገሩም ይገኛሉ፡፡ በዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስ ገልጠው የሚነጋገሩ፣ የቅዱሱን ተአምራት ወይም ገድላት የሚያነቡ፣ አንሥተው የሚመሰክሩ የዝክሩ ተሳታፊዎችም ሊገኙ ይችላሉ፡፡ ቤተ ክርስቲያንን እንዴት እናገልግል ብለው የሚጠበቡ፣ በወቅታዊ ጉዳዮቿ ላይ ተወያይተው ምን እናድርግ የሚሉ ወገኖችም የዝክርን መንፈሳዊ መልክ ጠባቂዎች ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

በአጠቃላይ ሲታይም አሁን አሁን የሚታየው አጓጉል የሆነው የዝክር አዘካከር በየጊዜው እየተፈታተነን ያለው ዓላማዊነት ምን ያህል እየሸረሸረን መሆኑን የምናስተውልበት ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ደግሞ ፍጹም መንፈሳዊ መልክ ለማስያዝ የሚተጉ በርካታ ክርስቲያኖች ሲታዩ ደግሞ ተስፋ እንዳንቆርጥ የሚያደርግ የመልካሙ ዝክር መልክ እንዳይለወጥ አብነት የሚያስቀርልን ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

በመሆኑም ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ሳናውቅ ወይም ተገደን በምንሳተፍባቸው አጓጉል መልክ ያላቸው ዝክሮች መንፈሳዊ መልክ እንዲይዙ ጥረት ማድረግ ይኖርብናል፡፡ ዝክር ጠሪዎቻችን ዝክራቸውን ከጊዜ ጊዜ በጎውን መልክ እንዲያላብሱት ማገዝ አለብን፡፡ አንዳንዴም ምን ማድረግ እንዳለባቸው ሳያውቁ የሚፈጽሙት ስለሚሆን በዝግጅታቸው ትሑት ሆነን በመሳተፍ ጭምር መርዳት አስፈላጊ ነው፡፡

# ከጋብቻ በፊት የሚኖር ግንኙነት ከቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ አንጻር እንዴት ይታያል?

*ወደ ቤተክርስቲያን መጣ ሔድ በማለት በበዓል፣ በመንፈሳዊ ጉባኤያት፣ በዕለተ ሰንበት በመገኘት "ክርስቲያን ነኝ" ለማለት በማልደፍርበት አካሔድ እመጣለሁ (እመላለሳለሁ)፡፡ በወጣትነት የዕድሜ ክልል ላይ እገኛለሁ፡፡ በእግዚብሔር ቤት መኖር የምመኝ የመንግሥት መስሪያ ቤት ሠራተኛ ነኝ፤ እናም ለማግባት ከፍተኛ ፍላጎት አለኝ፡፡ ብዙ ወንዶች ለጋብቻ ይጠይቁኛል፡፡ ለብዙዎቹ ‹‹የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን›› ብዬ እንዲጸልዩ እንዲተጉ ምክር እሰጣቸዋለሁ፡፡ አንድ ቀን ወደ መሥሪያ ቤት ስሔድ ታክሲ ውስጥ ከአንድ ወንድም ጋር ተዋወቅንና ስልክ ተለዋወጥን ከዚህ በኋላ እየተቀራረብን መጣን፡፡ ወደ ሥራ ቦታ ስንሄድም ሆነ ስንመለስ እየተጠባበቅን መሄድ ጀመርን በዚህ መሀል አንድ ቀን ወደ ሥራ እየሄድን ሳለ ስለትዳር ጉዳይ ተነስቶ እንድንጋባ ጠየቀኝ፡፡ ጥያቄውን ከመመለሴ በፊት እርሱ በጋብቻ ላይ ያለው አመለካከት ምን እንደሆነ ጠየቅሁት እርሱም ከጋብቻ በፊት ግንኙነት መፈጸም መልካም እንደሆነና ለጋብቻም ጥሩ መተዋወቅን እንደሚፈጥር፤ በአንጻሩ በምዕራባውያን ፺ ከመቶ በላይ የሚሆኑት ሰዎች ጋብቻቸውን የሚያፈርሱት በግብረ ሥጋ ግንኙነት አለመጣጣም የተነሳ እንደሆነ አክሎ ነገረኝ፡፡ እኔም እግዚአብሔር ባቀበለኝ መንገድ ‹‹ምዕራባውያኑ በቅድመ ጋብቻ ውስጥ በመኖራቸው ለምን ፍቺን መቀነስ ብሎም ማጥፋት አልቻሉም? እኔ ቅድመ ጋብቻን ዝሙት እንደሆነ ነው የማስበው›› ብዬ በጊዜው መለስ ሰጠሁት፡፡ ለመሆኑ ይህንን ጉዳይ ከቤተ ክርስቲያን አስተምሮ አንጻር ምን ትሉኛላችሁ?*

*ወለተ ማርያም*

ውድ እኅታችን ወለተ ማርያም ለችግርሽ መፍትሔ አገኛለሁ ብለሽ ወደ ዝግጅት ክፍላችን በመምጣትሽ በቅድሚያ እናመሰግናለን፡፡ በመቀጠልም ከጥያቄሽ በተረዳነው መሠረት ስለ ትዳር የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ በጥቂቱ እንደሚከተለው እናቀርባለን ተከታተይን ትዳር የሚመሠረተው ስለ ሦስት ነገር ነው፡፡

ትዳር ሰው ቤተሰቡን ትቶ ወይም ወላጆቹን ትቶ ከሚስቱ ወይም ከባሏ ጋር አንድ የሚሆኑበት ታላቅ ምሥጢር ነው፡፡ ትዳር የሚመሠረተው በሦስቱ ዋና ዋና ምክንያቶች በተለይ ከአምላክ ለሰው ልጅ በተሠጠው ትልቅ ስጦታ ውስጥ ነው፡፡ ‹‹ቤትና ባለጠግነት ከአባቶች ዘንድ ይወረሳሉ፤ አስተዋይ ሚስት ግን ከእግዚብሔር ዘንድ ናት፡፡›› (ምሳሌ ፲፱፥፲፬) እንዲል ጠቢቡ ሰለሞን ይህን ድንቅ ሥጦታ አምላክ ለሰው የሰጠውን ከቤተሰብ ሥጦታ ይልቅ የተሻለና የበለጠ መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡ እግዚአብሔር አምላክ በብሉይ ኪዳን የአዳምና የሔዋንን እንዲሁም የሌሎች ቅዱሳን አባቶች እና እናቶች ጋብቻ መባረኩ፤ በሐዲስ ኪዳን በዶኪማስ ቤት ተገኝቶ ውኃውን ወደ ወይን መቀየሩ ብሎም በሰርግ ቤት መገኘቱ የጋብቻን ክቡርነት የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ጋብቻ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ምሥጢር ነውና፡፡ ይህ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ምሥጢር ትዳር ለሰው ልጅ ስለ ሦስት ነገሮች ያስፈልጉታል፡፡

**፩. ለመረዳዳት፡-** ባልና ሚስት በአንድ ጐጆ ሲኖሩ የሚረዳዱበትን የሚተጋገዙበትን መንገድ ለማመቻቸት እርሱ ለእርሷ እርሷ ለእርሱ የሚያደርጉትን መተሳሰብ መመካከር ለማጠናከር ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹እግዚአብሔር አምላክም አለ ሰው ብቻውን ይኖር ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚረዳውን ረዳት እንፍጠርለት›› ዘፍ.፪፥፲፰ ይላልና፡፡ የእግዚአብሔር ሥጦታ ልዩ ከሚያደርጉት አንዱ ርዳታ ብቻ አይደለም የሚመች ጭምር ነው፡፡ እርሷ ለእርሱ ረዳት ስትሆን ልትመቸው እርሱ ለእርሷ ረዳት ሲሆናት የሚመቻትና ብቸኛነቷን የምትረሳበት መሆን እንዳለበት ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ያገባ ግን ሚስቱን እንዴት ደስ እንዲያሰኛት የዓለምን ነገር ያስባል… የተጋባች ግን ባልዋን እንዴት ደስ እንድታሰኘው የዓለም ነገር ታስባለች›› ፩ኛቆሮ.፯፥፴፫-፴፬ እንዲል ባል ለሚስቱ ለአካሉ የሚያደርገው ርዳታና ሐሳብ እርሷን ለማስደሰት የሚያደርገውን ጥረት እርሷም

ለርሱ ለባልዋ በምታደርገው የፍቅር መግለጫ በመተጋገዝ ማስደሰት እንደሆነም ሲገልጥ ጠቢቡ ሰሎሞን ‹‹ከልጅነት ሚስትህ ጋር ደስ ይበልህ›› ይላል ምሳ. ፭፥፲፰ ደስታው የመረዳዳት የመተሳሰብ መሆኑንም ይገልጽልናል። መረዳዳት ባለትዳሮች በአንድ ጣሪያ ሥር የሚኖሩበት ብዙ ነገሮችን በጋራ የሚፈጽሙበት ነው። ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ እንዳለው ‹‹በቤት ውስጥ ያለች ትንሿ ቤተ ክርስቲያን›› ናት።

**፪. ዘር ለመተካት፡-** እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ‹‹ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት፤ግዙአትም›› እንዳለ ዘፍ ፩፥፳፪-፳፰ ሰዎች ዘራቸውን እየተኩ ይበዙ ዘንድ አዝዟቸዋል። በትዳር ሒደት ውስጥ የአምላክ ሥጦታ ሆኖ የሚገኘው ታላቁ ተወዳዳሪና መተኪያ የሌለው ከእግዚአብሔር ብቻ የሚሰጠው የሁለቱ ፍሬ ልጅ ነው ‹‹መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር ነው ለመኝታቸውም ርኩሰት የለውም›› እንዳለ ሐዋርያው በዕብ.፲፫፥፬። ጋብቻ መልካም መኝታው ንጹሕ ነው ዘር ለመተካት እግዚአብሔር በተቀደሰ ጋብቻ ውስጥ የሚኖረው የልጅ በረከት ሥጦታው የርሱ ነው። ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊትም ‹‹እነሆ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው የሆድም ፍሬ የእርሱ ዋጋ ነው›› ይላል (መዝ. ፺፥፫።) ይህ የሁለቱም ዘር የሚሆን ልጅ የሚገኘው እግዚአብሔር በፈቀደው የትዳር ውጤት ነውና ስለዚህ ነገር ትዳር ይመሠረታል።

**፫. ከዝሙት ለመዳን፡-** የጋብቻ ሌላው ዓላማ ፍትወተ ሥጋን ለማሸነፍ ወይም ለመከላከል ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ከዝሙት ጠንቅ ለመከላከል ‹‹ስለ ዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው፤ለእያንዳንዲቱም ደግሞ ለራስዋ ባል ይኑራት›› በማለት ያስተምረናል (፩ኛ ቆሮ ፯፥፪-፱።)

በየቦታው ዓይኑ እየተቅበዘበዘ እንዳይፈተን የተሠራለት ሕግ በአንዲቱ እርሷም በአንዱ ወንድ ሊጸኑ ያስፈልጋል። ወደ ሌላ መመልከት ግን ዝሙት ነውና እንደሚያስቀጣ ፍርድ እንሚያመጣ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ይላል ‹‹እኔ ግን እላችኋለሁ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል›› ማቴ.፭፥፳፰ በማለት የቀደመውን ትእዛዝ ያጸናዋል። ፍትሐ ነገሥትም ሕግ ወደማፍረስ የሚያደርስ የፈቲውጾር በብዙ ሰዎች ቢጸና ጋብቻ መፈጸም እንዲገባ በአንቀጽ ፳፬፣ ክፍል ፩ ላይ ይነግረናል።

ስለዚህ የትዳር ትልቁ ሦስቱ ሀብት ሆነው የሰው ልጅ የሚጠቀምባቸው የሚያተርፍባቸው ከበሽታ ጤናን ከመርገም በረከትን የሚያገኝባቸው በተለይም ከአምላኩ ጋር ከሚያጣላው ይልቅ የሚያፋቅረውና የሚያስማማው በእንዲህ አይነት መንገድ በተመሠረተ የትዳር ሕይወት ሲኖር ነው።

> **እግዚአብሔር አምላክ በብሉይ ኪዳን የአዳምና የሔዋንን እንዲሁም የሌሎች ቅዱሳን አባቶች እና እናቶች ጋብቻ መባረኩ፤ በሐዲስ ኪዳን በዶኪማስ ቤት ተገኝቶ ውኃውን ወደ ወይን መቀየሩ ብሎም በሰርግ ቤት መገኘቱ የጋብቻን ክቡርነት የሚያረጋግጥ ነው። ጋብቻ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ምሥጢር ነውና።**

ትዳር የአንድ ቀን ደስታ የሚበሉት ምሳ፣ ቁርስ፣ እራት የግብዣ ምሽት አይደለም እስከ ሕይወት ፍጻሜ ያለ አንድነት ነው እንጂ። ‹‹ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ›› እንዳለ ማቴ.፲፱፥፮። ይህ ማለት ድንቅና ሰማያዊ ምሥጢር እንጂ በአካልም በመንፈስም የተለያዩ ሰዎች በአንድ ላይ የሚኖሩበት የደባልነት ኑሮ አይደለም።

ዛሬ ዛሬ የሚታዩት አንዳንድ ትዳሮች መሠረታቸው አንድነታቸውም ሥጋዊ መግባባት ላይ ብቻ ይሆንና በኋላ ላይ መሰለቻቸት አልፎ ተርፎ ታኘኮ እንደተጣለ ማስቲካ እስከ መርገጥ የሚደርስ ጥላቻ ውስጥ ይገባሉ:: ብዙዎች መጀመሪያ የቸኮሉበትን ነገር ሲያገኙ ፈተናው ይጠነክርና አንድነቱ ይፈራርሳል:: ስለዚህ እህታችን እንደገለጽሽው በቅድመ ጋብቻ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት በማድረግ የተመሠረቱ ትዳሮች መጨረሻቸው ፍቺ ነው የሚሆነው:: በአጠቃላይ በዚህ ዘመን በሁለቱም ላይ የሚታየው ትልቅ ችግር ከጋብቻ በፊት የሚደረግ የጾታ ግኑኙነት ሲሆን ውሎ ሲያድር ሁለቱንም ለተለያየ ችግር ሲዳርግ ይታያል:: እነሱም የሚከተሉት ናቸው::

## ፩. በመንፈሳዊ ሕይወት ላይ ሞትን ያስከትልባቸዋል

የቅድመ ጋብቻ ግንኙነት በእግዚአብሔር ዘንድ ዝሙት ነው፤ ኃጢአት ነው፤ ሞትም ነው:: ምክንያቱም የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና›› ሲል ቅዱስ ጳውሎስ አስተምሮናል:: ‹‹ሴሰኞችና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል›› ይላል ዕብ.፲፫፥፬:: ከዚህም በተጨማሪ ‹‹ ከዝሙት ራቁ›› ፩ኛ ተሰሎ ፬፥፫ ማለቱ ‹‹ዝሙት›› ቃሉ ራሱ ከትዳር ውጪ የሚፈጸምን ማንኛውንም የጾታ ግንኙነት የሚያመለክት ነው:: አንድ ወንድና ሴት ለመጋባት እቅድ ቢኖራቸውም ከጋብቻ በፊት የሚደረግ የጾታ ግንኙነት ኃጢአት መሆኑን ነው መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስረግጥልን:: ከዚህ ሌላ እንዲህ ዓይነት ግንኙነት በሥነ ልቡና ምሁራን ዘንድም ተቀባይነት እያጣ መምጣቱን ማስተዋልም ይገባል:: ቤተ ክርስቲያንም ከትዳር በፊት የሚፈጠረውን የሩካቤ ሥጋ ግንኙነቶች እጅግ ታወግዛለች በመድረኳም ቦታ የለውም::

## ፪. ማኅበራዊ ኑሮ ላይ የሚያስከትለው ችግር

ቅድመ ጋብቻ የሚፈጸም የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መሠረቱ በስሜት፣ በአካላዊ ቁመና መማረክ ላይ የተመሠረተ ይሆንና የጾታ ግንኙነቱ ከተፈጸመ በኋላ ችግሩ በተለይ በሴቶች ላይ ገዝፎ ይታያል:: ለምሳሌ በሴቷ ላይ በሚከተለው እርግዝና ምክንያት በማኅበረሰቡ ዘንድ የሚፈጥረው ተጽእኖ ቀላል አይደለም:: በዚህም ምክንያት ከማኅበረሰቡ ሐሜት እና ወቀሳ ለመሸሽ ያልተፈለገውንም ፅንስ ለማስወረድ በሚደረግ ጥረት ወደ ሕገ ወጥ ውርጃ ውስጥ ይገባል ነፍስንም ወደ ማጥፋት ይደረሳል:: ይህ ደግሞ ሕይወትን እስከማጣት ሊያደርስ ይችላል:: ከውርጃ ተርፎ ሕፃኑ ቢወለድ እንኳ አባት የሌለው ልጅ ባል የሌላት እናት የሚለው የማኅበረሰቡ ሐሜት በሕፃኑ የወደፊት ሕይወትም ሆነ በእናቲቱ ሥነ ልቦና ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ቀላል አይደለም::

ስለዚህ ውድ እህታችን እንደ ቤተ ክርስቲያን ልጅነትሽ ‹‹ምዕራባውያን›› ስለፈጸሙት ብቻ ትክክል ነው የሚልን ማስተባበያ ልትቀበይ አይገባም:: እንደ ሥልጣኔ ቆጥረውት እና ተቀብለው የተጓዙበት ራሳቸው ምዕራባውያኑ ምን ያህል የማኅበራዊና የመንፈሳዊ ኑሮ ቀውስ ደርሶባቸው እየተቸገሩ እንደሆነ ልታውቂ ይገባል::

በተጨማሪም የእውነተኛ ትዳር መሠረቱ ቅድመ ጋብቻ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት አይደለም:: ከጋብቻ በፊት የጾታ ግንኙነት የጀመሩ ሰዎች ከጋብቻ በኋላ የሚኖራቸው ሕይወት በእጅጉ ፈተና በዛበት ነው:: ነገር ግን ወደ ተቀደሰው ጋብቻ መቅረብ በኋለኛው ዘመንም በረከት ነውና ከቅድመ ጋብቻ የጾታ ግኑኙነት ርቀሽ ንጽሕናሽን ጠብቀሽ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን አክብረሽ ጋብቻ ልትፈጽሚ ይገባል:: ውድ እህታችን ለሁሉም እግዚአብሔር ዓላማሽን በልብሽ አጽንቶ ከተቀደሰው ሥርዓተ ጋብቻ ያድርስሽ:: እመቤታችን አትለይሽ::